# መብራቱን አብራው

እሺ። ይሄኛው ነው… [አንድ ወንድም፡ “ማይክሮፎንህ **ይህ** ነው” አለ።—አርታዒ።] ዋናው ይሄ ነው? አመሰግናለሁ፡ ወዳጄ። [“የሚሰራው ማይክሮፎን **ይህ** ነው።”] አዎ፡ ጌታዬ። እሺ። እዚያ ከኋላ ትንሽ ድምጽ እያስተጋባባቸው እንደነበር አይቻለሁ፡ ስለዚህ… እንደምን አደራችሁ፡ ወዳጆች። እዚያ ኋላ በደንብ ይሰማችኋል? [ጉባኤው፡ “አዎ” አለ።] አሰቆመው። አመሰግናለሁ።

2 እንደዚህ ያሉ የተከበሩ ምስክርነቶች ከተሰጡ በኋላ፡ ዛሬ ጠዋት፡ በዚህ መድረክ ላይ በመገኘቴ፡ በእርግጥም የታደልኩ ሰው ነኝ፥ ዛሬ ጠዋት እንደተደሰትነው—በረከቶችን ለእኛ ለማምጣት፡ እነርሱ በተናገሩት ላይ ጥቂት ለመጨመር ያክል ነው። አሁን፡ አንዳንዶቹ እንዳሰተዋልኩት በጣም…

3 [የድምጽ ማጉያው መዋቅር ድምጽ ይመልሳል። አንድ ወንድም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ይህንን፡ መሃል ላይ ማድረግ ያለብን፡ ይመስለኛል” አለ።—አርታዒ።] እሺ፡ ጌታዬ። አሁን ይሻላል?

4 እዚህ ካሉት አንዳንዶቹ ሰዎች ጋር፡ እንዴት እንደተናገሩ፡ እንዲሁም ሁሉም በሚባል ደረጃ… መልካም፡ እዚህ ላይ ያሉ ሁሉ እውነተኛ ግልጽ፡ ድንቅ ምስክርነት አስተላልፈዋል። ለጌታ የሚሰጠውን ግሩም ምስክርነት፡ እንዴት እንደማደንቀው!

አሁን ወደ ቃሉ እንገባለን።

5 በዚሁም ሳምንት፡ ሰዎችን፡ ለሁለት ወይም ለሦስት ሰዓታት እያስቀመጥኩ እንዲያዳምጡኝ፡ ላለማድረግ፡ በልቤ አስቤያለሁ። ወዳጆች፡ ለምን ያንን እንደማደርግ—ልንገራችሁ። ያልተማርኩ ነኝ፡ መናገርም የምችለው በመንፈስ ምሪት ብቻ ነው። አሁን፡ ትምህርት ያለው ሰው፡ እርሱም ደግሞ፡ በመንፈስ ሲመራ፥ ስለሚናገረው ነገር፡ በትምህርቱ ማስረዳት ይችላል፡ ሰዎች ስለሚናገረው ነገር እንዲያውቁ የሚያደርጉ ቃላትን ማውጣት ይችላል። ትምህርት ሳይኖረኝ፡ የተፈጥሮ ምሳሌዎችን በመውሰድና በመንፈስ ምሪት ባገኘሁት እገልጻለሁ። ይህም፡ አንዳንዴ ሰዎች በትክክል እንዲረዱት፡ በጣም ከባድ ያደርገዋል። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተመሳሳይ መንገድ፡ በተመሳሳይ አኳኋን እንዳደረገ እስካገኝ ድረስ ስለዚህ ጉዳይ በጣም ተረብሼ እንደነበር እናውቃለን።

6 መጥምቁ ዮሐንስን ብንመለከት፡ ስለ ትምህርት ደረጃው፡ ምንም ዓይነት መረጃ የለንም፡ እናም፡ ከ—ከምድረ በዳ ወጥቶ፡ ለዚያ ዘመን ቤተክርስቲያን፡ ለ—ለተሰበሰበው… ህዝብ መናገር ሲጀምር ግን እናስተውላለን። ሐሳቡንም እንዴት እንደገለጸው አይተናል። እርሱም፡ “እናንት የእባብ ልጆች” አለ። አያችሁ፡ ተላምዶት የነበረው ያንን ነው፥ ተፈጥሮንና ምድረ በዳውን፡ ሌሎች ቃላቶች፡ የሚያዳልጥ፡ የሚያስጠላና አታላይ የሆነን ነገር። አሁን፡ ሌላ ሰው ቢሆን ኖሮ ሌላ ቃል ይጠቀም ይሆናል ያንን ነገር ለመግለጽ ምናልባት “እናንተ አታላዮች”

ወይም ሌላ ቃል በተጠቀመ ነበር። ነገር ግን ዮሐንስ “እባብ” የሚለውን ቃል ተጠቅሟል። የተናገረውንም ሁሉም ሰው የተረዳው ይመስለኛል።

7 ከዚያም በመቀጠል እንዲህ አለ፡ “በልባችሁም፡ ‘**የእገሌ** ነን፡ ወይም **የእገሌ** ነን’ ማለትን አታስቡ፡ እላችኋለሁ፡ እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች” አያችሁ፡ አያችሁ፡ ሰለ ሌላ ታላቅ ነገር አይደለም። “እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች ሊያስነሳ ይችላል።” በተፈጥሮ ነው የገለጸው።

8 እንዲሁም፡ ደግሞ፡ “ምሳር በዛፉ ስር ተቀምጧል” አለ። አንድ የተማረ ወንድም ቢሆን ኖሮ፡ በዚያው መንፈሳዊ ምሪት፡ “ፈጽሞ ያጠፋዋል፡” ይል ይሆናል። እርሱ ግን፡ “ምሳር በዛፉ ስር ተቀምጧል” አለ። ያም ቢሆን፡ ማጥፋት ነው፡ አያችሁ፡ እርሱም—ያውቀው ነበር። ምንም ዓይነት ትምህርት ኖሮት ስለማያውቅ፡ የነበሩት አገላለጾች እነዚያው ብቻ ነበሩ።

ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

9 እዚህ የጸሎት ጥያቄዎች ይዣለሁ። አገልግሎቴም፡ እሱ ነው፡ ለታመሙት መጸለይ። እዚህ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉኝ፡ በጣም አሳሳቢ የሆኑ ጥያቄዎች አሉ። በዚሁም ውስጥ ብዙ እንዳሉ አውቃለሁ። ዛሬ ጠዋት፡ መታሰብ፡ የሚፈልግ ሰው ካለ? እንግዲህ፡ እጆቻችሁን ወደ እግዚአብሔር አንሰታችሁ፡ “አለሁ... ” በሉ። አሁን በምንጸልይበት ጊዜ ጥያቄዎቻችሁን በልባችሁ ያዙ።

10 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ እዚህ እጄ ላይ ያሉትን፡ ጥያቄዎቻቸውን፡ የጻፉትን ሰዎች ልመና ለማቅረብ፡ በቅዱሱ ልጅህ፡ በጌታ በኢየሱስ ሰም፡ አሁን ወደ ቅድሰናህ እየቀረብን ነው። በተለይም በዚያ አደጋ ክፉኛ የተጎዳችውን፡ የዚህን ወንድም ውብ የሆነች ትንሽ ልጅ አሰባለሁ። ጌታ ሆይ፡ ለዚያች ልጅ እጸልያለሁ። ለሌሎች ጥያቄዎች በሙሉ እጸልያለሁ። አሁን ደግሞ ከእኛ የተሰወሩትን፡ እጃቸውን ላነሱት ብቻ የሚያውቁትንም እናሰባለን፥ ነገር ግን አንተ ወሰን የሌለህ አምላክ ነህ፡ የሁላችንንም የልብ መሻትም ሆነ ጥያቄ ታውቃለህ። እንደምትመልሰልን እንጸልያለን። ቃል ሰለገባህልን፡ እናምናለን።

11 አሁንም አንተን ተሰፋ እያደረግን ሰንጠብቅ ጌታ ሆይ፡ እነዚህን የምናነባቸውን ጥቂት ቃላት፡ ወሰደህ፡ በመንፈስህ ለእኛ ህይወት እንድትዘራባቸው እንጠይቃለን። መንፈሰ ቅዱስ ወደ እያንዳንዳችን ይቅረብ፡ የቃሉንም ትርጉም ይግለጥልን። በኢየሱስ ሰም እንለምናለን። አሜን።

12 [አንድ ወንድም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ እንደሚሰራ ለማየት አንዴ መሞከር እንችላለን? ” አለ—እርታዒ።] አዎ፡ ጌታዬ፡ ወንድሜ፡ ና ችግር የለውም። ይሁን። አሁን ገጹን እየገለጥኩ ሳለሁ፡ አንድ ነገር ይዣለሁ...

13 ድሮ ማሰታወሻ—ሳልይዝ የመጽሐፍ ቅዱሰ ክፍሎችንና ሌሎች ነገሮችን፡ በቃሌ ማሰታወሰ እችል ነበር፡ ሆኖም ሃያ-አምሰትን ካለፍኩ ወዲህ፡ ያን ያህል አያሰኬድም። ሰለዚህ ጽፌ ማሰታወሰ ግድ ሆኖብኛል። አሁን እንግዲህ...

14 አሁንሰ ይሻላል? አሁንሰ በደንብ ይሰማችኋል? አይሰማም። ከኋላ ላይ፡ ራሳቸውን እየነቀነቁ ነው። ምናልባት... [አንድ ወንድም እንዲህ አለ፡ “ፊት ለፊትህ መቆም አለብህ።”—እርታዒ ።] መቆም አለብህ... [“ፊት ለፊት።”] ልክ ነው። ታዲያ **እንደዚህ** ቢሆንስ፡ አሁን ይሰማችኋል? **አሁንስ**፡ ይሻላል? ጥሩ። መልካም ነው።

15 አሁን ትኩረታችሁን ወ—ወደ ኢሳያስ 42፡ 1-7 ላይ፡ እና ደግሞ ማቴዎስ 4፡ 15-16 እንድታደርጉት እጋብዛችኋለሁ።

> **እነሆ ደግፌ የያዝሁት፡ ባሪያዬ፥ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት፡ ምርጤ፥ መንፈሴን በእርሱ ላይ አድርጌያለሁ፥ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል።**
>
> **አይጮኽም፡ ድምፁንም አያነሣም፡ በጎዳናም አያሰማም።**
>
> **የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፡... የሚጤሰውንም የጧፍ ክር አያጠፋም፡ በእውነት ፍርድን ያወጣል።**
>
> በ**ምድር ላይ ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ አይዝልም፥ ተስፋም አይቆርጥም፡ ደሴቶችም ሕጉን ይጠባበቃሉ።**
>
> **ጌታ... እንዲህ ይላል፡ ሰማያትን የፈጠረ፡ የዘረጋቸውም፥ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን፡ ያጸና፥ በእርሰዋ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ** እንጀራን፡ **ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እንዲህ ይላል፥**
>
> **እኔ እግዚአብሔር በጽድቅ ጠርቼሃለሁ፡ እጅህንም እይዛለሁ፡... እጠብቅሃለሁ፡ የዕውሮችንም ዓይን ትከፍት ዘንድ፡ የታሰሩትንም ከግዞት፥**
>
> **በጨለማም የተቀመጡትን... እስረኞችን** ከወኅኒዎች፡ **ታወጣ ዘንድ... ለሕዝብ ቃል ኪዳን፡ ለአሕዛብም ብርሃን... አድርጌ እሰጥሃለሁ።**

16 እና አሁን ደግሞ በቅዱስ ማቴዎስ 4፡ ከ 12 ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ ይህንን እናነባለን።

> **ኢየሱስም ዮሐንስ አልፎ እንደ ተሰጠ በሰማ ጊዜ፡ ወደ ገሊላ ፈቀቅ አለ፥**
>
> **... ናዝሬትንም ትቶ፡** መጥቶ **በዛብሎንና በንፍታሌም አገር፡ በባሕር አጠገብ ወዳለችው፡ ወደ ቅፍርናሆም መጥቶ ኖረ፥**
>
> **በነቢዩ** በኢሳይያስ **የተባለው ይፈጸም ዘንድ፡ እንዲህ ሲል፥**
>
> **የዛብሎን ምድርና፡ የንፍታሌም ምድር፡ የባሕር መንገድ፡ ከዮርዳኖስ ማዶ፡ የአሕዛብ ገሊላ፥**
>
> **በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና** ጥላ **ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው።**
>
> **ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ ሊሰብክ፡... እንዲህም ሊል ጀመረ፡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና፡ ንስሐ ግቡ።**

17 ጌታ ቃሉን ይባርክ! የዛሬ ጧት ርዕሴ፥ **መብራቱን አብራው** የሚል ነው። በሚቀጥለው አርባ-አምስት ደቂቃ ውስጥ፡ ለሚኖራችሁ ቀጣይ ቀጠሮ እንድትወጡ፡ በተቻለኝ ፍጥነት አቀርበዋለሁ።

18 ታውቃላችሁ፡ ሚስተር ማክ እናሊ፡ እዚህ ያለ ይመስለኛል። መኪናውን ውጭ አይቼዋለሁ። ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ አደን ፍለጋ ወደ አሪዞና በመጣሁበት ወቅት፡ ተቀምጠን ነበር። እዚህ ሱፐርስቲሽን

ተራራ አጠገብ ተቀምጠን ነበር። ስለ እሱ ለረጅም ጊዜ ሰምቼ ነበር፡ ስለ ሱፐርስቲሽንም የሚነገሩ ብዙ አፈ ታሪኮችንም ሰምቼ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ሳየው፡ አስታውሳለሁ፥ ገና አልነጋም ነበር፡ በምስራቅ በኩል ሱፐርስቲሽን በመባል የሚታወቅ፡ ትልቅ መንፈሳዊ ጥላ ተንጠልጥሎ ነበር። ስለ ሕንዳውያን ሰምቼ ነበር፡ እንዴት ወደዚያ እንደማይቀርቡ፡ እንዴት እንደሚፈሩ፡ በቀድሞ ዘመን እስፓኒያዊያን ወርቅ ሲያድኑ እንዴት እንዳንገላቷቸው ሰምቼ ነበር። ክፉ መናፍስት ይኖሩበታል ብለው ያምኑ ነበር። ይህ ሁሉ ጉጉቴን ቀሰቀሰው። ነገር ግን በመጀመሪያ፡ ሱፐርስቲሽንን ለማየት፡ የእጅ ባትሪ ብቻ ነበር ያለኝ።

19 ከዚያም ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ የፀሐዩ ግርማ፡ በጨለማው ላይ መንቀሳቀስ እስኪጀምር ድረስ ተመለከትኩ። ይህ ሲሆን፡ ጨለማውን ከብርሃኑ ለየው፡ ጨለማውንም ወደ ኋላ ገፈፈው። በመጨረሻም፡ ከተራራው ጫፍ በላይ፡ ከፍታዋ ላይ ወጣች፡ ሱፐርስቲሽንም ምን እንደነበረ በትክክል አሳየች። በራች ምን እንደነበረም አሳየች። ስለ ሱፐርስቲሽንም የነበረኝ ፍርሃትና ጭንቀት ሁሉ፡ ፀሐይ በኃይሏ ስታበራበት፡ ሁሉም ሸሽተው ጠፉ።

20 ፀሐይ በዚህ ምድር ላይ ካሉት የተፈጥሮ ብርሃኖች ሁሉ፡ የብርሃናት ንጉሥ ናት። የፈለገውን ያህል ሰው ሰራሽ ብርሃን ቢኖረንም፡ የፈለገውን ያህል ታላላቅ የኤሌክትሪክ ጨረሮችን ማምረት ብንችልም፥ ያች ፀሐይ ስትወጣ፡ ሌሎቹ በሙሉ ይደበዝዛሉ።

21 ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለውም ነገር እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሲወጣ፡ ባዶ እምነቶች፡ የሐይማኖት ተቋም አክራሪነቶችና መሰል ነገሮች ሁሉ፡ ይተንናሉ፡ መልክና ገጽታቸውም ምን እንደሚመስል ግልጽ ሆኖ ይታያል። እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ "ብርሃን ይሁን፡" አለ። ብርሃን የሚመጣው፡ እውነተኛው ብርሃን፡ የንጉሡ ብርሃን የሚመጣው፡ በእግዚአብሔር ቃል ነው። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ብርሃኑን፡ ከጨለማው ለየ። የተገለጠው፡ የእግዚአብሔር ቃልም፡ ሁልጊዜ ብርሃኑን ከጨለማው ይለያል።

22 ሰዎች **በዚህ**፡ **በዚያ**፡ ወይም **በሌላ** ነገር ሊነሱ ይችላሉ፥ ርዕዮተ ዓለሞች ሊነሱ ይችላሉ፡ ኮሚኒዝም፡ ፋሺዝምና፡ ሌሎችም ርዕዮተ ዓለሞች ሁሉ ሊነሱ ይችላሉ፥ ባዶ እምነቶች፡ ኑፋቄዎች፡ ማንኛውም ነገር ቢሆን፡ ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን ያ የመጽሐፍ ቅዱስ ንጉሥ ብርሃን ሲነሳ፡ ባዶ እምነቶችና ነገሮች ሁሉ... ነገር ግን፡ እያችሁ፡ መኖሩን እናውቃለን፡ ዳሩ ግን የተረጋገጠ ሆኖ፡ ብርሃንነቱን እስኪያረጋግጥ ድረስ፥ ያኔ ሁሉንም ሌላ ብርሃን ስለሚያጠፋው፡ በእርሱ ላይ የመከራከር መብት የለንም። ኢየሱስ፡ "የሰው ሁሉ ቃል ውሸት፡ የእኔ ግን እውነት ይሁን" አለ። ቃሉ ከሰው ቃላት ሁሉ፡ ከማንኛውም ነገር በላይ፡ የላቀ ነው። ቃሉ ብርሃን ነው።

23 በመጀመሪያ ዓለም ስትሸከረከር፡ እግዚአብሔርም ብርሃን እንደሚያስፈልግ ባወቀ ጊዜ፡ ጉም ጭጋግና ጨለማ የሞላበት እንደነበረ እናውቃለን። አሁን፡ ዘሩ ቀድሞውንም በምድር ውስጥ ነበረ፡ ምክንያቱም እዚያ ተክሎት ነበርና። አሁን ያንን ዘር ለማብቀል፡ ሕያውም እንዲሆን ለማድረግ ብርሃን አስፈለገው፡ ምክንያቱም ዘሩ ቀድሞውኑ እዚያ ነበረና።

24 በእያንዳንዱ ዘመን እንደሚሆነው ሁሉ፡ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ዘመን ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ነግሮናል። ለዚያ ዘመን ሕያው እንዲሆን ለማድረግ

የሚያስፈልገው ብቸኛው ነገር፡ በዚያ ቅዱስ ቃል ላይ የእግዚአብሔር ብርሃን መገለጥ ብቻ ነው። ብቻ... ? ... ብርሃኑ ቃሉን እስካገኘው ድረስ ይህንኑ ያደርገዋል። ቃሉ ሕይወት ያለው ከሆነ፡ ለዚያ ቀን የተሰጠ ተስፋ ከሆነ ሕያው ያደርገዋል።

25 በአንድ ወቅት ሰንዴን፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ እህልን ልትተክሉ ትችላላችሁ። አንዳንዶቹ ከሌላው ይልቅ ዘግይተው ይበቅላሉ፡ ምክንያቱም እንደየወቅቱ ይወሰናልና።

26 ሕግና ጸጋ፡ እንዲሁም ሌሎችም፡ በዘመናት ውስጥ ወደ ታች ሰንጓዝ፡ የእግዚአብሔር ቃል በየወቅቱ ይመጣል። በእያንዳንዱ፡ ጊዜም፡ በዘሩ ውስጥ—ያለውን ሕይወት በሚያሰራጨው የብርሃን መገለጥ ይበራል።

27 ዛሬ ፀሐይ የምታበራው፡ በእግዚአብሔር ቃል ነው፡ ምክንያቱም የምንዝናናባት ይህቺው ፀሐይ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ናትና። እርሱ፡ “ብርሃን ይሁን” ባለ ጊዜ የሆነው፡ በውጭ የምናየው ይህ የፀሐይ ብርሃን፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ ሌላ አይደለም።

28 እርሱ፡ “ብርሃን ይሁን” ብሎ፡ ብርሃን ባይሆን ኖሮስ? ያኔ የተናገረው እግዚአብሔር አልነበረም ማለት ነዋ። እግዚአብሔር፡ “ይሁን” ሲል፡ ይሆናል። በመሆኑም አሁን የምንዝናናባት ፀሐይ በዘፍጥረት የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ መሆኗን አወቅን።

29 የእግዚአብሔር የዘመኑ ብርሃን ልጁ መሆኑን እንገነዘባለን። አንደኛው s-u-n ፀሐይ ነበረ፥ ይህኛው ግን S-o-n ልጅ ነው። S-o-n ልጅ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እሱ... “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።” ዕብራውያን 13፡ 8፡ “እርሱ ትናንትና፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው” ይላል። ሁልጊዜም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በኖህ ውስጥ ክርስቶስ ነበር። በሙሴ ውስጥ ክርስቶስ ነበር። እንደተገፋ ንጉሥ፡ ወደ ከተማይቱ በተመለከተው በዳዊት ውስጥ የነበረው፡ ክርስቶስ ነበረ፥ ይህም፡ ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ፡ ልክ እንደ ዳዊት፡ የተገፋ ንጉሥ ሆኖ፡ በዚያችው ከተማ ላይ እያለቀሰ የተቀመጠው ክርስቶስ ነበረ። ሁልጊዜም የክርስቶስ መንፈስ ነው። ሙሉውም የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ታወቀ።

30 ከብርሃን ውጭ ምንም ሕይወት ሊመጣ አይችልም። ብርሃን የሚያፈራው፥ ብርሃን ሕይወትን ያፈራል። ተፈጥሯዊም ሆነ መንፈሳዊ፡ ከብርሃን ውጭ ሕይወት—ሕይወት ሊኖር አይችልም። መኖር አለበት።

31 ብርሃንም ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሲገለጥ ብርሃን ነው። እግዚአብሔር ዘሮችን ሁሉ እንደተከለ፡ እርሱም እዚህ የተቀመጠ ዘር ብቻ ነው።

32 አካሎቻችን እዚህ... እ፡ እ፡ ምንም ዓይነት ብርሃን፡ ምንም ዓይነት ሕይወት፡ ወይም ምንም ነገር ከመኖሩ በፊት በምድር ላይ ነበሩ፥ ካልሲየም፡ ፖታሽ፡ ፔትሮሊየም፡ እና ኮስሚክ ላይት ሆነ፡ ሌላው፡ እዚህ—እግዚአብሔር ምድርን በፈጠረ ጊዜ ነበር። ይህንም ወደ መኖር ለማምጣት የእጽዋትን ሕይወት ወይም የዛፍን ሕይወት፡ ወይም ሊኖር የሚገባውን፡ ማንኛውንም ሕይወት፡ ወደ መኖር ለማምጣት፡ የተነገረው ቃሉ ብቻ አስፈለገ።

33 ተፈጥሯዊም ሆነ መንፈሳዊ፡ ከብርሃኑ ውጭ፡ ምንም በሕይወት ሊኖር አይችልም፡ ቃሉም ብርሃንና ሕይወት ነው።

34 ነገር ግን ብርሃኑን ሲልክና ለሰዎች ሲያሳውቀው፡ ከዚያም የሚጠላ ከሆነ፡ ታዲያ ስለዚያ ምን ይባላል? ዛሬ ጠዋት፡ ልንነጋገርበት የፈለግነው ይሄንኑ ነው፥ ብርሃኑን በተላከላቸው ሰዎች፡ ይህን ብርሃን መጠላት፡ ያኔ እንደነበረው ሁሉ ውድቅ ማድረጋቸውን ነው። "እነሆ በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ ባሪያዬን።" እርሱ ለአሕዛብ ብርሃን ነው። እርሱ ለዓለም ብርሃን ነው። እርሱ የዓለም ብርሃን ነበረ፡ ነገር ግን ተጠላ። የሚያሳዝነው ክፍልም ይሄው ነው።

35 እግዚአብሔር ብርሃኑን በሚገልጥበት ጊዜ ሁሉ ያንኑ ሁኔታ ያጋጥመዋል፡ ዓለም እራሷ ያንን ብርሃን ትጠላዋለች። ለምን? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትክክል ተጽፏል። በእያንዳንዱ ዘመን፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ዘመን የሚሆን የቃሉን ድርሻ መድቧል፡ ያንንም ቃል እንዲገልጥ ሁልጊዜም አንድን ሰው ይልካል።

36 ኢየሱስ፡ መሲሕ ሆኖ እንደሚመጣ፡ ለአራት ሺህ ዓመታት ትንቢት ተነግሮለት ነበረ። እርሱም ሲመጣ፡ የመሲሑን የተሰፋ ቃል ሁሉ ተርኳል። ነገር ግን የዓለም ሰዎች፡ አብያተ ክርስቲያናት፡ እና የመሳሰሉት፡ ስለ እርሱ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፡ ምክንያቱም ይህን እንዲያውቁ ወደ ከለከላቸው ሌላ ነገር ውስጥ አስቀድመው ገብተው ነበረና። ታዲያ—ሰው ዝም ብሎ...

37 ለምሳሌ ተፈጥሯዊውን ክፍል እንውሰድ። እግዚአብሔር በፈጠረለት፡ በዚያ የፀሐይ ብርሃን ውስጥ ሊመላለስ፡ የተወለደ አንድ ሰው፡ እናም፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ዓይኖቹን በመጨፈን፡ ወደ ምድር ቤት ቢሮጥና፡ በሩን ቢዘጋ፡ መጋረጃውን ቢሰብ፡ ፀሐይ እያበራች መሆኗን ለመቀበል ፈጽሞ እምቢ ቢልስ? ጥቅሞቿን ይክዳል። የሚያሞቀውን ጨረሯን፡ ሕይወት-ሰጪ ምንጯን ይክዳል። ወዴት እየሄደ እንደሆነ ከየት እንደመጣ እንደሆነ፡ ለማየት እንዲያስችለው የምታሰራጭለትን ብርሃን ይክዳል። ያንን ይክዳል። መጋረጃዎቹን ወደታች ለሳበው ሰው፡ ወይም ወደ ምድር ቤት ሮጦ ብርሃኑን ሁሉ፡ በየቦታው ለዘጋ፡ ፀሐይ እያበራች መሆኗን ለመቀበል በቀላሉ እምቢ ላለ ለዚያ ሰው ምን ትሉታላችሁ? ያ ሰው ምናልባት የስነ ልቦና ችግር አለበት። ሁሉም ሰው ያውቃል ። ተፈጥሮአዊ አእምሮ በዚያ ሰው ላይ የሆነ ችግር እንዳለ ይነግራችኋል፡ የሆነ ነገር፡ ሆ—ሆኗል... የሆነ ነገር በእርሱ ላይ ተከሰቷል። አመክንዮዎች ጎድለውበታል።

38 እንግዲህ፡ እኛ እየኖርን ባለው በዚህ ዘመንም ሁኔታው እንደዚሁ ነው፡ አንድ ሰው በሆነ—ባልሆነ ምክንያት ራሱን ሲሸፍን፡ ዛሬ እንደሚያበራው የወንጌልን ብርሃን በእውነት ላለመቀበል ነው። አንድ ሰው ሆን ብሎ ከእርሱ ሲርቅ፡ ወደ አንድ ነገር ውስጥ ገብቶ መጋረጃውን ወደ ታች ሲሰብ፡ "አላምነውም፡" ሲል፡ በዚያ ሰው ላይ የሆነ ችግር አለ። ከዚህ በምንም መንገድ መራቅ አይቻልም። የሆነ ችግር አለበት። የሆነ ነገር አጋጥሞታል። ዛሬም እንዲህ ዓይነቱ ነገር በጣም፡ በጣም ብዙ መሆኑን እንገነዘባለን።

39 አሁን፡ ኢየሱስ በመንፈስ ምሪት የተነገሩ የነቢያት ምስክርነቶች ሁሉ ነበረ። በዘመኑም ሊሆን የተነገረው ትንቢታቸው ሁሉ፡ በእርሱ ዘመን ወደ ብርሃን ወጣ። እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የነበረውን፡ ስለ እርሱ ትንቢት

የተነገረለትን እያንዳንዱን የቃሉ ሻማ አበራ። “ድንግል ትፀንሳለች።” ጸነሰች። መልካም። “ሰሙም ድንቅ መካር፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት ይባላል።” ነበረ። “የዕውሮችም ዓይኖች ያያሉ።” አይተዋልም። ስለ እርሱ ትንቢት የተነገረው ሁሉ፡ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ተፈጽሟል።

40 ታዲያ ሰዎች ያንን ለምን ማየት አቃታቸው፡ ያ... አሁን ወደ-ኋላ በሚያሳይ መስተዋት እየተመለከትን ስለሆነ፡ ለእኛ እንግዳ ይሆንብናል። መንገዱን ሁልጊዜ ወደ ኋላ የምትመለከቱ ከሆነ፡ አደጋ እንደሚገጥማችሁ ግን፡ ታውቃላችሁን? ከፊታችን ያለውን እንመልከት።

41 ያንኑ ሲያደርጉ ነበረ። ያንን ያደረጉበት ምክንያት፡ በሌላ ብርሃን ብልጭታ ውስጥ ይኖሩ ስለነበር ነው። በሌላ ዘመን ብርሃን ነጸብራቅ ውስጥ ይኖሩ ነበረ።

42 ወዳጆች ሆይ፡ ዛሬም በዓለም ላይ ያለው ችግር ይህ ነው፡ ምክንያቱም በሌላ ዘመን በበራ የብርሃን ነጸብራቅ ውስጥ ለመኖር እየሞከርን ስለሆነ ነው። ነጸብራቅ ሐሰተኛ ብርሃን ነው።

43 በመንገድ ላይ እንደሚታይ የውሃ ሽታ ነው። በመንገዱ ላይ ስንጓዝ የውኃ ሽታ እናያለን። የፀሐይ የሐሰት ገጽታ ነው። እዚያም ስትደርሱ፡ ከሐሰት በቀር ምንም የለውም። ምክንያቱም፡ በፀሐይ ነጸብራቅ ውስጥ መመላለስ አትችሉም፡ የውኃ ሽታ ስለሆነ፡ ሁልጊዜም ለምንም የማይሆን ነገር ያሳያችኋል።

44 ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው እንዳልሆነ ሊነግሯችሁ ሲሞክሩ፡ ወደ ውኃ ሽታ እየመሯችሁ ነው። በቃ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትገቡም ቤተ ክርስቲያንን ስትቀላቀሉ፡ የሆነ ቀዝቃዛ የሐይማኖት መግለጫ ውስጥ ወይም እንደዚያ ያለ ነገር ውስጥ ስትገቡ፡ በዓለም ውስጥ ከነበራችሁት የተለየ፡ ምንም አዲስ ነገር እዚያ የለም።

45 ልንገራችሁ። የመንፈስ ቅዱስን የሚያሞቅ ጨረር በእናንተ ላይ የሚያመጣውን፡ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት የሚያደርጋችሁን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን የወንጌል ብርሃን አልቀበልም አትበሉ። በሌላ ዘመን ነጸብራቅ ውስጥ ለመመላለስ አትሞክሩ። አሁን፡ ያ ነጸብራቅ በዚያኛው ዘመን ትክክል ሊሆን ይችል ይሆናል፡ ለእነርሱ ትክክል ሊሆን ይችል-ይሆናል።

46 በጌታችን በኢየሱስ ዘመንም እንደዚያው መሆኑን አረጋግጧል። እርሱ የዚያ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን ነበረ። እርሱ ብርሃን ነበረ። የተሰፋውን ቃል ሊያረጋግጥ ወደ ምድር እስኪመጣ ድረስ እርሱ ብርሃን አልነበረም። ታውቃላችሁ፡ እርሱ በዚያ፡ “ዮሐንስ የሚያበራና የሚፈነጥቅ ብርሃን ነበረ፡ እናንተም ለጥቂት ጊዜ በብርሃኑ ደስ ብሏችሁ ልትመላለሱ ወደዳችሁ” አለ።

47 በእርግጥም፡ ዮሐንስ ከመወለዱ ሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በፊት፡ እንዲህ ተብሎ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮለት ነበር፡ “በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ፡” ተባለ። ከዚያም ደግሞ፡ ከነቢያት መጨረሻ የሆነው ሚልክያስ፡ እርሱ ከመምጣቱ አራት መቶ ዓመት በፊት፡ በ-... በሚልክያስ ምዕራፍ 3 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ “እነሆ መልእክተኛዬን እልካለሁ፡ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፡” አለ።

48 ዮሐንስ ያንን የተጻፈ ቃል ሕያው እያደረገ፡ እዚህ ምድር ላይ ነበረ። እርሱ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ነበረ፡ ሁልጊዜም... እንዲሁም ከመሲሑ

በፊት መንገዱን እያዘጋጀ ነበረ። ኢየሱስም፡ “እርሱ ያ የሚያበራና የሚነድ ብርሃን ስለነበረ፡ በብርሃኑ ልትመላለሱ ወደዳችሁ፡” አላቸው።

49 ዮሐንስም፡ “አሁን እኔ ላንስ፡ ብርሃኔም ሊጠፋ ይገባዋል፡ ምክንያቱም (ለምን? ) ስለ እኔ ትንቢት የተነገረለትን ጊዜዬን አገልግያለሁና። እርሱን ስሙት! እርሱ ነው። እርሱን ተከተሉት” አለ። በዚያ ዘመን ሕያው ሆኖ መገኘቱ፡ ይህን አረጋግጧል።

50 አሁን፡ አይሁድ በእውነተኛው ብርሃን ውስጥ እያመለኩ እንደሆነ አሰበው ነበረ። ውድቅ እያደረጉት ያለውን ይሄንኑ አምላክ፡ እያመለኩ እንደሆነ ይመስላቸው ነበረ። እያመለኩት ነው ብለው ያሰቡትን እርሱን፡ እራሱን እየሰቀሉት ነበረ። እግዚአብሔርን ራሱን እያፌዙበትና፡ የሕዝቡ መሳለቂያ እያደረጉት ነበረ፡ እናመልከዋለን ብለው የሚያሰቡት ያንን አምላክ።

51 ወንድማችን ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደተናገረው፡ እኛ ከምናሰበው በላይ፡ ዘግይተን እየኖርን ስለሆነ፡ ይህንን በአክብሮትና በፍርሃት፡ ነገር ግን ብርሃንን ለማምጣት ልናገረው። ከነዚህ ቀናት በአንዱ የሆነ ነገር ይከሰታል፡ በጣም የረፈደ ይሆናል። ሰዎች ምን እያደረጉ እንደሆነ እንኳ ሳያውቁ፡ የአውሬውን ምልክት ይቀበላሉ። ኢየሱስ፡ “ዕውርን ዕውር ቢመራው፡ ሁለቱም በጉድጓድ ውስጥ ይወድቃሉ” አለ። እኛም ከምናሰበው በላይ ዘግይተን እየኖርን ነው። ብዙ ቅን ሰዎች ምን እያደረጉ እንደሆነ እንኳ ሳያውቁ፡ ያንን ይከተላሉ።

52 ዳሩ ግን አሁን ብርሃን የሚበራበት ሰዓት ቀርቧል፡ የወንጌል ብርሃን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን ራሱን እየገለጠ ነው። ያንን ለዚህ ቀን መድቦታል። ለዚህ ቀን ቃል የገባላቸው ነገሮች በዚህ ቀን መፈጸም አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ይህንን የማትቀበል ከሆነ፡ እግዚአብሔር ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆችን ማስነሳት ይችላል። መልእክቱን ያደርሳል፡ ምክንያቱም ከድሮም አድርጎታልና። ሁልጊዜም ያደርገዋል።

53 ሰዎች በአባቶች ትውፊት፡ በብርሃን ውስጥ እየተመላለሱ እንደሆነ ያስባሉ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ይኸውላችሁ፡ በብርሃን ነጸብራቅ ውስጥ እየተመላለሱ ነው፡ ያንኑ ብርሃን አይደለም፡ እያመለክነው ነው የሚሉትን ያንኑ ብርሃን ውድቅ አድርገዋል።

54 ማን እንደነበረ ስራዎቹ ራሳቸው በሚገባ አረጋግጠዋል። ኢየሱስ ራሱ፡ እንዲህ አለ፡ “በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ ይመሰክራሉ። ስለ ኃጢአት የሚኮንነኝ ማን ነው? ” እርሱ፡ “እኔ የተናገርኩትን ማናቸውንም ነገር፡ ወይም ያቀረብኩትን ማንኛውንም የይገባኛል ጥያቄ፡ የሰማዩ አባት በእኔ በኩል እንዳላጸደቀው ማረጋገጥ የሚችል ማን ነው? ” የዘመኑ ብርሃን እርሱ መሆኑን አረጋግጦላችኋል፡ ምክንያቱም ይህ መሲሕ እንዲህ እንደሚሆን ትንቢት ተነግሮ ነበርና፡ እነሆም ሕያው ሆኖ ፈክቷል፡ ዳሩ ግን ትውፊቶቻቸው ከቃሉ እውነተኛ ብርሃን ለይተዋቸው ነበር።

55 ፈሪሳውያን፡ ሰዱቃውያን፡ ሄሮድሳውያን፡ እና ማናቸውም ቢሆኑ፡ በዘመናት ሁሉ እንዳደረጉት፡ ዓለምን በውጥንቅጥ ውስጥ ስለተዋት፡ እውነተኛውን ብርሃን ማየት አልቻሉም። ዓይኖቻቸውን አሳወረው። በነጸብራቅ ውስጥ

ለመመላለስ ለምደው ነበር፡ “በሚቀጥለው ቀን **ይሄ** ይሆናል፡ ነገ ደግሞ **ይሄ** ይሆናል። **ይሄንን** እንቀላቀላለን፡ **ያም** ይሆናል። **ያንን** እንቀላቀላለን።” የሐሰት የውኃ ሽታ መሆኑን ደርሰንበታል።

56 ኢየሱስ ክርስቶስ ድሮም እንደነበረው ሁሉ፡ ዛሬም፡ ለሰው ልብ እውን ነው። ኃይሉና ሕያው ህልውናው ምንጊዜም እንደነበረው ሁሉ ዛሬም እውን ነው። “እነሆ፡ ትንሽ ጊዜ አለ፡ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም። ኮስሞስ፡ ‘የዓለም ሥርዓት፡’ ከእንግዲህ አያየኝም። እናንተ ግን፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር ስለምሆን፡ በውስጣችሁም ስለምኖር፡ ታዩኛላችሁ። እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡ ከዚህም የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና” አለ።

57 ይህ ታላቅ ተስፋ ዛሬ ነው። ዓለም ከአቅም በላይ ታውራለች፡ ዳሩ ግን “እናንተ ግን ታዩኛላችሁ” የሚልም አለ፡ ዛሬም ልናገኘው የምንሞክረው ያንን ነው። ሙሉ ወንጌል፡ ማለት፡ ኢየሱስ ክርስቶስን በትንሣኤው ኃይል፡ እንዲሁም በተሰፋዎቹ ሙላት ሁሉ መግለጥ ማለት ነው፥ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸውን እነዚህን ነገሮች፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲገልጣቸውና ትክክል እንዲያደርጋቸው ነው፡ ያደርገዋልም። አዎ፡ ጌታዬ።

58 በሚያደርገው ሥራና በ—በቃሉ በሚገባ የተረጋገጠ ነበረ፡ ነገር ግን አንዳቸውም ማመን አልፈለጉም። ብርሃኑ ቃል መሆኑን አረጋገጠ! ቃሉ እንዲህ አለ፡ “መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ።”

59 ነገር ግን ይኖሩባቸው የነበሩት ትውፊቶቻቸው፡ የሌላ ዘመን ነጸብራቅ ነበሩ! እነርሱም፡ “እኛ ሙሴን እናምናለን፥ እኛ የምናምነው ሙሴን ነው። አንተ ከወዴት እንደመጣህ አናውቅም። ትምህርትህን ከየት አገኘኸው? አንተ **ይህ** መሆንህን በምን ማረጋገጥ ትችላለህ” አሉ?

60 መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ አንብበው ቢሆን ኖሮ፡ ሥራዎቹ ማን እንደነበረ ይመሰክሩ ነበረ። እያነበቡት ነበረ፡ ዳሩ ግን ማየት አልቻሉም። “ሥራዎቼ ስለ እኔ ያሳውቃሉ።”

61 ሰው የሚታወቀው በመታወቂያዎቹ ነው፡ በእግዚአብሔር ቃል መታወቂያዎች፡ በእግዚአብሔር ቃልና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተላከ ከሆነ። በእያንዳንዱ ዘመንም ያው ነው! ሁልጊዜም እንደዚያው ነበረ።

62 በትናንትና ብርሃን መኖር አንችልም። የትናንትና ብርሃን ታሪክ ነው። ስለ እርሱ ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ትናንትና ባበራች ፀሐይ ዛሬ መሞቅ አትችሉም። ዛሬ አብያተ ክርስቲያናትን የገጠማቸው ችግር ይሄው ነው። ሰዎቹንም የገጠማቸው ችግር ይሄው ነው፡ ትናንትና በሆነው ነገር ለመኖር እየሞከሩ ነው። በስእል እሳት መሞቅ አትችሉም። በጭራሽ አይቻልም፡ በውስጡ አንዳች ሙቀት የለውምና። የትናንትና ፀሐይ በውስጧ ምንም ሙቀት የላትም።

63 የፀሐይ ብርሃን ወደ ምድር የሚላከው፡ ተፈጥሮ ላይ፡ ወደፊት ለሚመጣው መከር እህልን ለማብሰል ነው። እያንዳንዱ ቀን አዲስ ፀሐይን ያመጣል። ዛሬ የምታበራው ፀሐይ፡ በካናዳ፡ ስንዴውን እያሳደገች ነው፥ እንግዲህ፡ ያቺው ፀሐይ፡ ከ... ከዚያ የበለጠ ፀሐይ ባይኖራት ኖሮ፡ በሚመጣው ሐምሌ ወይም

ነሐሴ፡ እህሉን ፈጽሞ ልታበስለው አትችልም ነበር። እህሉን ለማሳደግ፡ በየቀኑ ስታድግና ስትበስል፡ ይበልጥ ጠንካራና ኃይለኛ ያደርጋታል።

64 አሁን እህሉ፡ እራሱ፡ መብሰል ይጀምራል፡ እህሉ ያድጋል፡ ከእህሉ ጋር አብራ የምትቆይ ከሆነ፡ እህሉን ብቻ ያፋፋዋል። ፀሐይዋ፡ በየቀኑ እየበረታች ስትሄድ፡ በዙሪያው ያለው ገለባ፡ ካ—ካልሲየሙ እና ሌሎች ንጥረነገሮች ይገባሉ፡ ፀሐይ እየጠነከረች በሄደች ቁጥር፡ ፍሬውን በትክክል ያፋፋዋል።

65 ዳሩ ግን በነሐሴ ወር የምታበራውን ፀሐይ ወስዳችሁ፡ ዛሬ በስንዴው ላይ ብታደርጓት፡ ትገድለዋለች። በጭራሽ፡ ያንን ማድረግ አትችሉም። በወቅቱ መምጣት አለበት። የእግዚአብሔር ስንዴና እህል እንዲሁ ልክ እርሱ ባለበት ወቅት፡ በወቅቱ መድረስ አለበት። ዳሩ ግን ፀሐይ... እንግዲህ፡ ዛሬ በምትኖረው ፀሐይ፡ ማለቴ ዛሬ በምትበራው ፀሐይ፡ ስንዴው ይሞታል፡ ፍሬዎችም፡ ይሞታሉ። እየመጣ ያለው መከሩ እየበሰለ ነው። እህሉ ከብርሃኑ ጋር መብሰል አለበት።

66 ዛሬ ያለው ችግር ግን፡ ቤተ ክርስቲያኒቷ ሰብሏ መብሰል አትፈልግም። ልክ በሙዲ ዘመን፡ በሳንኪ፡ በፊኒ፡ በኖክስ፡ በካልቪን ዘመን እንደነበረው ሆና መቆየት ትፈልጋለች። እነርሱ በዚያ ዘመን፡ የዘመኑ ጥሩ ብርሃን ነበሩ።

67 ይህ ግን ሌላ ዘመን ነው። ይህ ሌላ ዘመን ነው። ይሄ የወንጌል ልቀት ነው፥ ወደ ብስለቱ እየመጣ ነው። በመሆኑም ሉተር በተናገረው፡ ዌስሊ በተናገረው፡ ወይም ከነርሱ መካከል አንዳንዶቹ በተናገሩት ውስጥ መኖር አንችልም። የምንኖረው ለዚህ ዘመን በተነገረው ብርሃን ውስጥ ነው። እኛ ሰባተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ ነን፡ ሦስተኛ ወይም አራተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን አይደለም። ሰብሏ መቀበል አለባት። ካልተቀበለች፡ ትረግፋለች እርባና ቢስ ይሆንባታል። ከብርሃኑ ጋር አብሮ የሚጓዝ ከሆነ ሰብሉ በብርሃኑ ይበስላል።

68 ታዲያ ቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ የእያንዳንዱን ዘመን እንጀራ ልታመጣ ይገባታል፡ ይህም፡ ኢየሱስ “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ ሕያው ይሆናል፡” ብሎ እንዳዘዘ ነው።

69 የሚያስፈልገን እንጀራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። ይህም የእግዚአብሔር ዕቅድ መገለጥ በሙሉ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ መገለጥ ነው። በእርሱ ላይ ምንም አንጨምርም፡ ወይም ከእርሱ ምንም አንቀንስም፥ ማንም ይህንን ቢያደርግ፡ ስሙ ከሕይወት መጽሐፍ ይደመሰሳል። በዚህ ላይ የምንጨምራቸው ምንም ዓይነት የሐይማኖት መግለጫዎች አያስፈልጉንም። ልክ መሆን በሚገባው መንገድ ተጽፏል። እኛ በእርሱ ላይ ምንም አንጨምርም፡ ከእርሱም ምንም አንቀንስም፡ እንዳለ ሆኖ እንሰብከዋለን፡ እግዚአብሔርም፡ ይገልጠዋል። የሰጠውን እያንዳንዱን ተስፋ፡ ልክ እንዳለው ይገልጠዋል። እኛ ከእርሱ ልንቀንስ ወይም በእርሱ ላይ ልንጨምር አይገባንም። እንዳለ ተዉት።

70 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ሰዎች በዚያን ዘመን እንደነበረው ዓይነት፡ ዛሬም፡ በመጠኑም ቢሆን ወደ ኋላ ተመልሰው በነጸብራቅ ውስጥ ለመኖር ሲሞክሩ እናያለን። ስንዴ እንደሚበስል ቤተ ክርስቲያን መብሰል አለባት፡ “ሰው በእንጀራ ብቻ ሳይሆን፡ በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ፡ በሕይወት እንጀራ ሕያው

ይሆናልና።" የቃሉን የተወሰነ ክፍል ብቻ አይደለም፥ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ፡ የእያንዳንዱን ዘመን ቃል! ሁልጊዜ እዚያው ተቀምጣችሁ ባቄላና ድንች አትብሉ። በእግዚአብሔር ታላቅ እራት ሙሉ ገበታ፡ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በእርሱ ወደ—ለመደሰት፡ ስለተሰጠው ኃይልና መንፈስ ሰንገባ፡ አብረው የሚሄዱ ሌሎች ነገሮችም አሉ። "የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። እኔ ሕያው ነኝና፡ እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ።" ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጣቸው ተስፋዎች፡ ነገር ግን ዛሬም ሰዎች ወደ ኋላ አልፎ ወደ ሄደ ሌላ ዘመን ለመሄድ ሲሞክሩ እናያለን።

71 የሉተር ዘመን፡ ታላቅ ዘመን ነበረ። እርሱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ስህተት አየ፡ ቁርባኑን አየ። ያ፡ ያ ወጣት ቄስ፡ ይህ ስህተት እንደሆነ አየ፡ "ይህ ቃል በቃል የክርስቶስ አካል አልነበረም፡" እነርሱ የባረኩት አንድ—ቁራሽ እንጀራ ነበረ። እርሱም፡ "ወይኑ ቃል በቃል ደሙ አልነበረም፡" ነገር ግን ደሙን የሚወክል መሆኑን አየ። በመሆኑም የዚያ ጊዜው ሰዓት ደርሶ ስለነበር ያንን ነገር ተቃወመው። ምንም ያህል ቄሶች ቢኖሯቸው፡ ወይም ከዚያም በላይ ምንም ቢኖራቸውም፡ ብርሃኑን ሊያበራ የሚችልን ሰው እግዚአብሔር አገኘ። አሜን። እርሱም፡ "በእምነት መጽደቅ" የሚለውን ተቀበለ፡ የሉተራውያንንም ዘመን ብርሃን እንዲያበራ አደረገ። ያም ከተፈጸመ በኋላ፡ ጊዜውን ጨርሶ አለፈ።

72 በመቀጠል ቤተ ክርስቲያን ከኃጢአቷ ርቃ፡ የምትቀደሰበት ሌላ ጊዜ መጣ። እዚያ ከእንግሊዝ የመጣ አንድ ትንሽ የአንግሊካን ሰው፡ ጆን ዌስሊ መጣ፡ እርሱ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን አባል ነበረ፡ ዳሩ ግን የወንጌሉን ብርሃን አየ። ያ የፊላደልፊያ ዘመን የሚመጣበት ሰዓት ነበረ። እርሱም በመጣ ጊዜ፡ ሁለተኛውን የጸጋ ሥራ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መቀደስን ሰበከ። በብርሃኑ ፊት ሊቆም የሚችል ምንም ነገር አልነበረም። ልክ እንደ ሉተር አክራሪ ተደርጎ ተቆጥሮ ነበረ፡ ዳሩ ግን ሌሎቹን ሁሉ ተቃወመ፡ ብርሃኑንም አበራ፡ ምክንያቱም የዘመኑ ብርሃን ነበረና። ብርሃኑን ሊያበራ የሚችልን ሰው፡ ጆን ዌስሊን፡ እግዚአብሔር አገኘ።

አገኘ… እንዲሁም ለዚያ ዘመን ብርሃኑን ያበራውን፡ ሉተርን አገኘ።

73 ከዚያም የጴንጤቆስጤ ወንድሞች መጡ። እነርሱም በዘመናቸው ተመለሱ፡ ወደ የስጦታዎችን መመለስ መጡ፡ በልሳኖች የመናገርን፡ የመፈወስን፡ እንዲሁም ሌሎች ስጦታዎችን፡ ለቤተ ክርስቲያን መልሰው አቃኑ። አሁን፡ እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያደርጋሉ እንዳለው ልክ በዚያው መንገድ አደረጉ፡ ባደረጉ፡ ጊዜም፡ ገለጡት። ያ ፍጹም ትክክል ነው።

74 ነገር ግን ከዚያ አልፈን እንደተጓዝን ተገንዝባችኋልን? እኛ አሁን በሙሽራይቱ ዘመን ውስጥ ነን፡ በምርጫው ጊዜ ውስጥ ነን፡ እንደሚኖረን አስቀድሞ በተባለልን (የሙሽራይቱ) ዘመን ውስጥ ነን። ኢዩኤል 2፥28 እንዳለው፡ "ኩብኩባ የተወውን ሁሉ፡ ተምች የተወውን—የተወውን ሁሉ፡ አንበጣ ሁሉ፡ ተምች የበላውን ሁሉ።"

75 ከእነዚያ ድርጅቶች እያንዳንዱ፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ሰባት ማኅተሞች አንብባችሁ ከሆነ፡ ከእነዚያ ተሃድሶ አራማጆች እያንዳንዱ ሄደው ቃሉን ሰብከዋል፡ ዳሩ ግን የሆነ ነገር ትተው አልፈዋል። ታዲያ ከተሃድሶ አራማጆች በኋላ፡ እንዲሁም ብርሃኑ መደብዘዝ ከጀመረ በኋላ ምን አደረጉ? ወደ ላቀው

ብርሃን ከመጓዝ ይልቅ፡ አደራጁት። ባደራጁትም ጊዜ፡ "እኛ **ይሄኛው** ብርሃን እናምናለን። ብርሃኑም **ይሄኛው** ነው! **ይሄው** ነው።" ምን አደረጉ? ዌስሊ በትክክል መጣና ከእነርሱ ርቆ ሄደ።

76 ዌስሊ ምን አደረገ? ከእርሱ በኋላ ተደራጁ፡ ወንድሙ—ወንድሙም፡ ጆን እና—እና ቻርልስ፡ እንዲሁም፡ አስበሪና እነዚያም መጡ፡ ከዘመናቸውም በኋላ፡ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን የተባለውን አደራጁ። ምን አደረጉ? የላቀውን ብርሃንን ጠሉት። ዝም ብለው፡ "ብርሃኑ **ይህ** ነው። **ይሄው** ነው" አሉ።

77 ከዚያም ጴንጤቆስጤዎች መጡና፡ እግዚአብሔር አሁንም የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንደሚያወርድ አሳዩአቸው። እነርሱ የካዱትን የመፈወስ ኃይሉን፡ አሁንም እንደሚያወርድ አሳዩአቸው። እነርሱስ ምን አደረጉ? ሌላ ብርሃን ስለሆነባቸው፡ ከእነርሱ ርቀው ሄዱ።

78 አሁንስ እንዴት ነው? ስልሳ ዓመታት ገደማ አልፈናል፡ ጴንጤቆስጤዎችም ተደራጅተዋል፡ "እኛ **ይህ** ነን፡ እኛ **ያ** ነን" ብለዋል፡ እግዚአብሔርም ርቆ ሄዷል፥ ወደዚያ ወጥቷል፡ ከዚያም ቡድን ውስጥ ሙሽራን፡ ምርጦችን፡ እያወጣ ነው። ይህ ማለት፡ ከዚህ በኋላ ሌላ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ፈጽሞ አይኖርም። የፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ዌስሊ ነበረ። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ደግሞ የጴንጤቆስጤ ድርጅት ነው፡ ይህም ሁሉም በቀጥታ ወደ አውሬው ምልክት እየተንደረደሩ ነው። ቀደም ሲል ወንድማችን እንደተናገረው፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። እውነቱ ይህ ነው። ትክክል። እነርሱ፡ እነዚያ ድርጅቶች ሁሉ፡ በላቀው ብርሃን ለመጓዝ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ነው። እራሳቸውን አደራጅተው፡ "ይህንን እናምናለን፡" ይላሉ። እግዚአብሔር አንድ ነገር ሲያደርግ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መርምሩት።

79 ፈሪሳውያን፡ "እኛ ደርሰንባታል" አሉ። ሰዱቃውያን፡ "እኛ ደርሰንባታል" አሉ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበረች! እግዚአብሔር ቁልፉን ከፈተና ብርሃኑን አሳየ። ሁልጊዜ እንደነበረው ሁሉ ውድቅ ተደረገ።

80 የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሉተርን ተቃወመች። ዌስሊ ሉተርን ተቃወመ። ጴንጤቆስጤም ዌስሊን ተቃወሙ።

81 መንፈስ ቅዱስም ዛሬ ጴንጤቆስጤዎችን እየተዋቸው ነው። ልክ እንደሌሎቹ መደበኛ ቀዝቃዛም እየሆናችሁ መጥታችኋል። ሰው ሁሉ ያንን ማየት ችሏል። እወዳችኋለሁ። እስከማውቀው ድረስ፡ ለመጽሐፍ ቅዱስ በጣም የቀረባችሁ እናንተ ናችሁ፡ ለዚህ ነው ከእናንተ ጋር የሆንኩት። ነገር ግን፡ ስሙ፡ አይኖቻችሁን ክፈቱ የምንኖርበትንም ዘመን ተመልከቱ! ቁልፉ ዳግም የሚዞርበት፡ ብርሃንም የሚበራበት፡ እንዲሁም ዛፍ የሚወጣበት ዘመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፡ በሚልክያስ 4፡ "ልኮ ከህዝቡ ጋር የነበረውን የመጀመሪያውን እምነት መልሶ ያቃናል" ይላል። ይህን ተስፋ ሰጥቷል። ከዚህ በፊትም ሁሌ ሲያደርግ ኖሯል። ቃሉን ላከ፡ ቃሉም ወደ ነቢያት ስለመጣ ነቢያት መጡ፡ ቃሉንም ተቀብለው ሕያው አደረጉት።

82 በየዘመናቱ የነበሩ ድርጅቶች፡ እንዲሁም መዋቅሮች አልተቀበሏቸውም፡ ዛሬም ያንኑ ያደርጋሉ። እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ እንዳደረገው ዛሬም አንድ ሰው ማስነሳት ይችላል። ድርጅቶችን ከቶ አስነስቶ አያውቅም። ማንኛውንም

የታሪክ ምሁር ጠይቁ፡ ታሪክንም መርምሩ፥ አንድ ድርጅት ሲደራጅ፡ እዚያው ይሞታል እንጂ ዳግም አይነሳም። እግዚአብሔር ለግለሰቦች ይናገራል። አዎን።

83 እግዚአብሔርም በመጨረሻዎቹ ቀናት ዳግም ሊያደርገው ተስፋ ሰጥቷልና፡ ያንንም ያደርገዋል። እግዚአብሔር ቃል የገባውን፡ ያደርጋል፡ ለዘመኑ የተገቡትን የተስፋ ቃላት የሚያረጋግጥ ብርሃንን ያበራል። ኢየሱስ፡ “በ—በሎጥ ዘመን እንደ ነበረ፡ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ እንዲሁ ይሆናል” አለ። አይታችኋል፡ ምን እያደረጉ እንዳሉ ተመልከቱ። ያሕዌ ምን እንዳደረገ፡ ተመልከቱ፡ አባታችን ሁሉን ነገር ቦታ ቦታውን አስይዟል።

84 እነሆ ሎጥ በዚያ በዓለም ውስጥ፡ በዚያ ታች በሰዶም፡ በኃጢአት ሁሉ ተሞልቶ፡ ለብ ባለ ሁኔታ ይገኛል። እርሱንም የሚሰብከው መልእክተኛ ደግሞ፡ እነሆ።

85 የተመረጡት፡ የወጡት፡ ተስፋውን የያዙት፡ ልጅን በእውነት የሚጠባበቁት፡ የአብርሃም ቡድን ደግሞ እነዚህ አሉ። ሎጥም፡ ወንድ ልጅን ይፈልግ ነበር፡ ዳሩ ግን አብርሃም ይፈልገው በነበረው መልክ አልነበረም። ምን ሆነ? ይህ ከመሆኑ በፊት፡ እግዚአብሔር ወርዶ ራሱን በሥጋ ተገለጠ፡ እርሱም ቃል መሆኑን አረጋገጠ፡ ምክንያቱም፡ “የእግዚአብሔር ቃል ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፡ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል።” ኢየሱስም፡ “የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም፡ እንዲሁ ይሆናል” ብሏል። እነዚህ ተስፋዎች መለኮታዊ ናቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ከንፈሮች የተነገሩ ናቸው። ሰማይም ምድርም ያልፋሉ እንጂ፡ እነርሱ ከቶ አያልፉም። እግዚአብሔር አሁንም ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት ይችላል። ኦህ፡ አዎን!

86 ልክ እንደ እስራኤል፡ በጉዟችን ላይ ነን። እስራኤል፡ በጉዟቸው ውስጥ፡ በየቀኑ አዲስ መና መልቀም ነበረባቸው፡ አዲስ መና ይወርድ ነበርና። እኛ በሉተር ብርሃን ውስጥ መኖር የለብንም፡ በ—በዌስሊ ብርሃን መኖር፡ ወይም በጴንጤቆስጤ ብርሃን መኖር የለብንም። በሌላ ዘመን ውስጥ ነን፡ አዲስ መና።

87 ያን መና አሳድረው ለማቆየት ቢሞክሩ ምን ይሆን ነበር? ይበላሽ ነበር። ይገድላቸውም ነበር። እጅግ ብዙ መንፈሳዊ ሙታን የሆኑ፡ ክርስቲያን-ተብዬዎችን ያሉን ለዚህ ነው። የሌላን ቀን ነጸብራቅ እየበሉ ነው። የተበላሸን መና እየበሉ ነው። በሰንዴው ላይ እንዳለው ገለባ፡ ወደ ሰንዴው ውስጥ ካልገባ፡ ከሰንዴው ላይ ይወድቃል። ብርሃንም ተቀባይነት ሲያጣ፡ ሊደረግ የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ወደ ጨለማነት መቀየር። የሌሊቱ ማናቸውም ክፍል፡ ብርሃኑን ለማየት ፈቃደኛ ካልሆነ፡ ተመልሶ ወደ ጨለማ ይገባል። በወንጌልም ውስጥ እንዲሁ ነው፡ በየዘመናቱም እንዲህ መሆኑ ተረጋግጧል። እኛም እየኖርን ያለነው በዚያ ዘመን ውስጥ ነው።

88 የትናንትናው መና የተበላሸ ነው። ሰዎች፡ “ከአርባ ዓመታት በፊት፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** አድርጌ ነበር” ሲሉ እሰማለሁ። ልክ ነው፡ ሆኖም ስለ ዛሬው ታዲያ ምን ይባላል? ስለተቀጣጠለችው ቤተክርስቲያንስ? ስለ ትላንትና እናወራለን፡ ስለ ዛሬዋ ቤተክርስቲያንስ? ስለ እናንተ በግላችሁስ? ምክንያቱም፡ የትላንትናው ለዛሬ አይሆንም። ለትላንትናው ልክ ነበር።

89 የሉተር መልእክት፡ ልክ እንደ ዮሐንስ፡ በዘመኑ ብርሃን ነበር ዳሩ ግን ታላቅ ብርሃን ተነሳ። ሉተርም እንዲሁ ታላቅ ብርሃን ነበር፡ ለተወሰነ ጊዜም ተደሰተንበት ነበር፡ ነገር ግን የእርሱን ያሚያጠፋ ሌላ ብርሃን ተነሣ። መደረግ-የነበረበት ከእርሱ ጋር መዋሃድ ነበር፥ ወደ ፍጹሙ እንጀራም ተሻገረ፡ ወደ ፍጹሙ የእግዚአብሔር መና ሄደ። ሆኖም ምን አደረጉ? ድርጅት አቋቋሙ። ሰው ጣልቃ ገባበት። እግዚአብሔር ከሚመራ ይልቅ፡ ሰውና መዋቅሮቹ ገቡበት፡ አሳወሩትም።

90 ኦህ፡ ይህ የሙሽራይቱ ዛፍ፡ ዛሬ እየተገረዘ ነው። ፍሬ የማያፈራ ማንኛውም ቅርንጫፍ ይቆረጣል። ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 15 ላይ፡ እንደዚያ ብሏል። አሁን እየሆነ ያለው ነገር፡ እየተቆረጡ፡ እየተገረዙ መሆናቸውን አይተናል።

91 አስታውሱ፡ የዛፉ ዋና ልብ ያለው ልክ በዛፉ መሀል ላይ ነው። ፍሬ ሁልጊዜ የሚበስለው፡ አንድ ዛፍ ፍሬ የሚያፈራበት የመጨረሻው ቦታ፡ ልክ በጫፉ ላይ ነው፡ ምክንያቱም በዘሩ ውስጥ ካለው የሕይወት ማዕከል የሚመጣው ትኩስነት ነውና።

92 የሙሽራ ዛፍ ነው። ኢየሱስ ሙሽራው ነበረ፡ እርሱ ዛፍ ነበረ። ቆረጡት። እርሱ በኤደን ገነት ውስጥ የነበረው የሕይወት ዛፍ ነበረ። ሊያላግጡበት፡ ቆረጡትና በሮማውያን ዛፍ ላይ ሰቀሉት። እርሱ ምን አደረገ? እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን አስነሳው። እነሆ ዛሬም የሙሽራው ዛፍ አለ፥ የጀመረው ገና ጥንት፡ ወደ ኋላ በጴንጤቆስጤ ቀን ነው።

93 አድምጡ፡ የቤተክርስቲያን ሰዎች የሆናችሁ ሰዎች! ቤተክርስቲያን መቼም በኒቂያ፡ ሮም አልጀመረችም። የጀመረችው በኢየሩሳሌም ነው፡ በጴንጤቆስጤ ቀን፡ ቤተክርስቲያንን ጀመረ። ከዚያም ምን አደረጉ? ድርጅት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፥ እግዚአብሔርም ቅርንጫፎቹን መቁረጡን ቀጠለ። ከዚያም ሉተራንን አደራጁ፥ ቅርንጫፎቹን ቆረጠ። ዌስሊ፥ ቅርንጫፎቹን ቆረጠ። ጴንጤቆስጤ፥ ቅርንጫፎቹን ቆረጠ። እስከሚመጣ ድረስ...

94 ነገር ግን እግዚአብሔር የሙሽራ ዛፍ ይኖረዋል! "ተምች የበላውንና ኩብኩባ የበላውን ሁሉ፡ እመልሳለሁ፡" ይላል ጌታ። ሚልክያስ 4 እንደሚነግረን በጴንጤቆስጤ ቀን እንደነበረው ወደ መጀመሪያው እምነት እንደምንመለስ ይነግረናል፡ "ወደ አባቶች እምነት።" ይህ እንደሚመጣ እናምናለን። አሁን ጊዜው እንደደረሰ አምናለሁ። ቅርንጫፎቹ ጠውልገዋል ደርቀዋልም፡ ከዛፉም ላይ ይወስዷቸዋል፡ ይህም ፍሬው ልክ በዛፉ ጫፍ ላይ ራሱን ማፍራት ይችል ዘንድ ነው። ኦህ፡ ማይ!

95 እነዚህ ብርሃኖች ሁሉ ልክ ናቸው። ዛሬ ቤተክርስቲያን ያ ብርሃን ሲደመር ዛሬ የተቀበለችው ናት። መከሩን ለመጨረስ ነው። ዛፉ ራሱ፡ ወይም... ስንዴው ከብርሃኑ ጋር መብሰል እንዳለበት፡ ተረድተናል፡ ራሱን ከቅጠል ወደ ፍሬ፡ ከፍሬም ወደፊት እያሳደገ። ከብርሃኑ ጋር ይበስላል። የሌሎች ዘመናት ብርሃን የዚህን ዘመን ምስክርነት ብቻ ይይዛል። የሉተር ብርሃን—የዌስሊን ብርሃን ምስክርነት ይዞ ነበር። ዌስሊ የጴንጤቆስጤን ብርሃን አወጣ። ያው አንድ ብርሃን ነው፡ በብርሃኑ የበሰለ ብቻ ነው። ሰዎቹ ማየት ብቻ ቢችሉ!

96 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ አንድ ትንሽ አንቀጽ እያነበብኩ ነበር፡ የእንግሊዝ ንግሥት፡ (ይህችኛዋ ንግሥት ሣትሆን) ሌላኛዋ ንግሥት፡ እንዲህ ያለ ግሩም

ወረቀት ወደሚያመርት አንድ የወረቀት ኩባንያ ለማየት ሄደች። ከኩባንያው ፕሬዚዳንት ጋር ቃለ ምልልስ ስታደርግ፡ እየመራት አስጎበኛት። ያ ግሩም ወረቀት እንዴት እንደሚሰራ ማየት ፈለገች። እየመራት ታላላቆቹን ማተሚያዎችና ነገሮችን ሁሉ አሳያት። በዚያ ዘመን፡ ወረቀት የሚሰሩት ከጨርቃ ጨርቅ ነበር። ያንን በሚገባ እናስታውሳለን። ስለዚህ ወደ አንድ ክፍል ገብቶ በሩን ከፈተ፡ ከጨርቅ ቁርጥራጭ በቀር ምንም አልነበረም። ንግሥቲቱም፡ በመገረም፡ "እነዚህ ቆሻሻ ነገሮች ምንድን ናቸው፡" አለች?

97 ያ ሰው... የኩባንያው ፕሬዚዳንት የሆነው ያ ሰው፡ "ያ፡ ትናንት ልብስ፡ ነበረ። ይኸው፡ ቆሽሿል። አንጥለውም፡ ነገር ግን የነገ ወረቀት ነው" አላት።

"ይህ አልገባኝም፡" አለች።

እርሱም፡ "ነገ ይገባሻል" አላት።

98 ስለዚህ እነዚህን ጨርቆች በማተሚያው ውስጥ ሲያሳልፏቸው፡ በተወሰነ የማጽዳት ሂደት፡ እና—እና ማለፍ በነበረበት በተወሰነ ነገር፡ ሂደት፥ ሲወጣ፡ የሚያምሩ የወረቀት ሉሆች ነበረ። ፕሬዚዳንቱ ንግሥቲቱ ፈጽሞ የማታውቀውን ነገር ሊያሳያት አሰበ። የርሷን ምስል አድርጎበት፡ ወደዚህ ውብ ወረቀት አተመው። ንግሥቲቱ ስትቀበለው፡ ትናንት ቆሻሻ ጨርቅ በነበረው ላይ፡ የራሷን ምስል አየች፡ ምክንያቱም በተወሰነ ሂደት ውስጥ አልፏልና።

99 ኦህ፡ ሉተር፡ ዌስሊ፡ እና ሁሉም፡ ያንን ማየት ቢችሉ ኖሮ፡ የትናንቱ ነገር በሂደት ውስጥ ሲያልፍ ብቻ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ባዩ! መንፈስ ቅዱስ ብርሃኑን ሲገልጥ፡ ከጽድቅ ወደ ቅድስና፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ እና አሁን ደግሞ የክርስቶስ መምጫ ወደሆነው ወደ መጨረሻው ሰዓት፥ በውስጡ ምስል አለው፡ የንግሥቲቱ ሳይሆን፡ የሰማይ ንጉሥ ራሱን የሚወክልበት፡ ቤተክርስቲያን ይበልጥ ወደ አናሳው ቡድን በተጠጋች ቁጥር፡ አገልግሎቱም እርሱ የነበረው ዓይነት አገልግሎት መሆን እንዳለበት።

100 በሉተር ዘመን የሞቱት፡ ልክ፡ በፒራሚዱ ግርጌ እንዳሉት ናቸው፥ የፒራሚድ ትምህርት ሆኖ አይደለም፡ ነገር ግን ለምሳሌ ያህል ብቻ ነው።

101 ያ ፒራሚድ እጅግ ፍጹም ነው፡ ከእናንተ መካከል እዚያ የነበረ ካለ። የምላጭ ስለት እንኳን ማሳለፍ፡ አትችሉም። እነርሱ—እንደምናውቀው፡ ምንም ዓይነት ማጣበቂያ ቡኮ አልነበራቸውም። የሰነ ህንፃ ጥበቡ እጅግ ታላቅ ነበር! አሁን፡ የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ የለም ጠፍቶባቸዋል። የት እንዳለ እያውቁም። አሁን ያ የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ሲመለስ፡ ልክ እንደ ቀሪው ይሆናል፡ ክፍት ሆኖ ከተተወው ድንጋይ ጋር ይዋሃዳል። የማዕዘኑን ራስ ድንጋይ በላዩ ላይ ብታስቀምጡት፡ በዚያው ልክ መሆን አለበት።

102 ኢየሱስም ሲመለስ፡ እድፍ ወይም የፊት መጨማደድ የሌለባትን፡ የታጠበች ቤተክርስቲያንን ያገኛል፡ አገልግሎቱም እርሱ የነበረው ዓይነት አገልግሎት ይሆናል። የማዕዘኑን ራስ ድንጋዩን ይመልሠዋል።

103 እዚህ እንደ እጄ፡ በጥላ ውስጥ። ጥላ ነው፡ ይበልጥ እጄ እየቀረበ ሲመጣ ይበልጥ ይጨልማል... **እዚህ** ኔጌቲቭ ነው፡ **እዚህ** ፖዘቲቭ ነው። ኔጌቲቭ እና ፖዘቲቭ ሆኖ፡ ይበልጥ ችፍግ እያለ ይሄዳል፥ እየጨለመ፡ እየጨለመ፡

እየጨለመ፡ በመጨረሻም አብሮ ይጋጠማል፡ ኔጌቲቭ እና ፖዘቲቭ አንድ ይሆናሉ።

104 ቤተክርስቲያን እና ክርስቶስ እንደ ሙሽራ፡ አንድ ላይ ሲዋሃዱ፡ በእርሱ ውስጥ የነበረው ያው መንፈስ በእርሷ ላይ ይሆናል፥ ቤተክርስቲያን ከጽድቅ፡ ከቅድስና፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ወደ መጨረሻው ዘመን ስትመጣና፡ አሁን ለጌታ መምጣት ራሷን ስታዘጋጅ አንድ ይሆናሉ።

105 ኦህ፡ የጴንጤቆስጤ ወንድሜ ሆይ፡ በዚያ ውስጥ ሻካራው ክፍል አትሁኑ። ከቃሉ ጋር አንጾባርቁና እያንዳንዱን ክፍል እመኑ። ዛሬ ሲካሄድ እንደምናየው፡ ወደ እነዚህ ኢዝሞችና ነገሮች አትግቡ። በዚህ አትገረሙ፡ ምክንያቱም የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ፡ በቅርቡ፡ "አባ፡ አባት፡" እያለ ይመጣልና፡ "አምላኬ! አምላኬ!" አዎ፡ ያንን በሙሉ ልቤ አምናለሁ።

106 አያችሁት? ምን ማለቴ እንደሆነ ገብቷችኋል? አሁን ክርስቶስ የትናንቱን ጨርቆች፡ ሉተራንን፡ ሜቶዲስትን፡ ፕሬስባይቴሪያንንና የመሳሰሉትን፡ እየወሰደ፡ በሂደት ውስጥ እያሳለፋቸው ነው። ምን ዓይነት ሂደት? የመንፈስ ቅዱስ ሂደት፥ እነርሱ የነበራቸውን፡ ሲደመር፥ ቤተክርስቲያንና ክርስቶስ በአንድነት አንድ ሲሆኑ፡ የራሱን መልክ እስኪያትምበት ድረስ እያደረገው ነው። እግዚአብሔር ሆይ፡ ይሁንልን! እንደምታዩት ተስፋ አደርጋለሁ። ካያችሁት...

107 ይህ አንድ ታሪክ ያስታውሰኛል፡ ያ—ታላቁ የዌልሽ ሪቫይቫል በነበረበት ጊዜ። እዚህ ሀገር ውስጥ ያሉ አንዳንዶቹ ታላላቅ ሰዎች ሄደው የዌልሽን ሪቫይቫል፡ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ለማየት አሰቡ። በየትኛው ሕንፃ ውስጥ እንደሚካሄድ፡ ለማየት፡ ሄዱ። ዌልሽ ሲደርሱ፡ ዞር ዞር እያሉ፡ ሕንፃው የት እንደሆነ መጠየቅ ጀመሩ። አንድ ደስተኛ የሆነ አጭር ኦፊሰር ትንሿን ቶሚ ባርኔጣው አጥልቆ፡ ዱላውንም እንደዚያ እያሽከረከረ፡ በማዕዘን ላይ ቆሞ አዩ። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ወደ እርሱ ሄደው፡ እንዲህ በማለት ጠየቁት፡ "ጌታዬ፡ የዌልሽ ሪቫይቫል በየትኛው ሕንፃ ውስጥ እንደሚካሄድ ሊነግሩኝ ይችላሉ? "

108 እርሱም መልሶ፡ "አዎ፡ ጌታዬ፡ እኔ ነኝ! እኔ ራሴ ነኝ!" ለምን? በውስጡ ያለውን የዌልስን—የዌልሽን መነቃቃት ደስታና ብርሃን እያንጸባረቀ ነበር።

109 ዛሬም የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን፡ እንዲህ መጠየቅ አለባት፡ "ትናንት፡ ዛሬም፡ እስከ ዘላለምም፡ ያው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው? " የወንጌሉ ብርሃን የዚህን ዘመን ቃል ይዞ ሊያበራ ይገባል፡ በድሮ ዘመን እንደነበረው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ለአገሩ መገለጥ አለበት።

110 ሰውየው ራሱ የዌልሽ ሪቫይቫል እስኪሆን ድረስ በዌልሽ ሪቫይቫል እጅግ ተሞልቶ ነበር።

111 እኛም ለዚህ ዘመን በተመደበልን የቃሉ ኃይል ውስጥ እርሱን—እስክናንጸባርቅ ድረስ በክርስቶስ እጅግ ልንሞላ ይገባናል። ወንድሞች፡ በዓለም ነገሮች አትዋጡ፡ አትዋጡ፡ ከእርሱ በሚያርቋችሁ በእነዚህ ጭንቀቶች። ከወንጌል ጋር ጽኑ። እያንዳንዱን ቃል ጠብቁ! አንዳንድ አባት እንደሚሉት ነገር ወደ ኋላ አትመለሱ። በዚህ ዘመን ይሆናል ብሎ ኢየሱስ ወዳለው ነገር አሁኑኑ እንሂድ። አዎ፡ ጌታዬ። እኛ የዚህ ዘመን ብርሃን፡ ወንጌልን የምንገልጥ ልንሆን ይገባናል። ሉተር የዘመኑ ብርሃን ነበረ። ዌስሊ በዘመኑ ብርሃን፡ ጴንጤቆስጤም የዘመኑ ብርሃን ነበረ። ሆኖም ግን፡ እኛ አሁን

መንገዱን ይበልጥ ወደፊት ሄደናል፡ ወደተጠራችው፡ ወደተመረጠችው፡ ወደ ሙሽራ እየመጣን ነው። አስታውሱ፡ ይህ ከሆናችሁ፡ ልክ እንደዚያ ኦፊሰር ናችሁ፡ እርሱ በውስጡ ነበረች።

112 አስታውሱ፡ ይህ ሰባተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ነው፡ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን። እንደ ራዕይ 3 መሠረት፡ ክርስቶስን አልተቀበሉትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው ከእያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ዘመን፡ የሎዶቅያ ዘመን ከሁሉም የከፋ ነበር። እርሱን አባረረችው፡ አልተቀበለችውም፡ በውጭ አስቀመጠችው።

113 ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ወደ ሮም ከመሄዳቸው በፊት፡ ከሮም ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄዳቸው በፊት፡ ባለፈው ሌሊት፡ ጨረቃ ስትጨልም አያችሁ? ኢየሩሳሌም፡ እጅግ ጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ናት፥ ጨረቃ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት፡ ሁልጊዜም የፀሐይን ብርሃን ታንጸባርቃለች፡ ፀሐይ ከሌለች፡ እርሷም ትጨልማለች። ይህንን እዚህ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ሰዬዋለሁ፡ ከሦስት ወይም ከአራት ዓመታት በፊት፡ በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ፡ በመቶዎችና በሺዎች በሚቆጠሩ ቤቶች ውስጥ ላሉ ቤተክርስቲያናት አሳይቻለሁ። ምንድን ነበረ? ጥላ። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሲወጣ ይህ የመጀመሪያው ነው፡ ወደዚህ ለመመለስ፡ በ—በጳውሎስ ሰምና፡ የመሳሰሉት ለመምጣት፡ በእነዚያ ቦታዎች ውስጥ አለፈ፥ ወንዙን ለመሻገር፡ መባረክ ነበረበት፡ እና የመሳሰሉት። ወንዙ—ወንዙ ምን በረከት ያስፈልገዋል?

114 ዛሬ በምንኖርበት የቤተክርስቲያን ዘመን ያለው ችግር ምንድነው? አይታያችሁም ወይ? እግዚአብሔር በሰማያት እያወጀው፡ በቃሉ እያወጀው፡ በወረቀት ላይ እያወጀው፡ በሰዎቹ መካከል እያወጀው ሳለ? ዓይኖቻችሁን ከፍታችሁ ዘመኑን ማየት አትችሉም? ስለ እውነት የሚመሰክሩት እነዚህ ናቸው። የዘመኑ ብርሃን ይህ ነውና።

115 ይህን ታላቅ የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴ ተመልከቱት፡ አሁን ወደዚያ ካውንስል እያመራ ነው፡ የአውሬው ምስል እየሰራ ነው፡ ልክ በራዕይ 17 ላይ፡ ይሆናል እንዳለው። እናንተ የጴንጤቆስጤ ሰዎች ዝም ብላችሁ ተቀምጣችሁ ወደዚያ ልትገቡ ነው? የማስገደጃው ሰዓት ደርሷል።

116 አሁን መብራታችሁን የምታበሩበትና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልና ኃይል የምታበሩበት ጊዜ ነው።

117 ብዙዎቹ የጴንጤቆስጤ ወዳጆቼ ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱና ከነገሮች ጋር በተቀመጡበት በዚህ ጊዜ፡ ይህ ደስ እንደማይላችሁ አውቃለሁ፡ "በጣም መንፈሳዊ ስሜት ተሰማኝ፡" ይላሉ። ለእኔ፡ ያ ስህተት—ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ይቃወማል። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ይሁን። አዎ፡ ጌታዬ። ጊዜው አሁን ነው። እነዚህ ታላላቅ እንቅስቃሴዎች ሲሆኑ አይተናል... ኦህ፡ ለሥጋዊ ዓይን ጥሩ ይመስላሉ፡ በትክክል።

118 ቀያፋ ለካህናቱ ሲገልጥላቸው የነበረው፡ በዚያን ዘመን፡ በዚያ ዘመን ሁሉ፡ ጥሩ ይመስል ነበር። ኢየሱስ ግን ቃሉን ሕያው የሚያደርግ ብርሃን ነበር፡ ካውንስላቸው እና ልዩ ልዩ ነገራቸው ግን ዓይኖቻቸውን አሳወረ። "ተውአቸው፡ ዕውር ዕውርን ቢመራ፥ ሁሉም ወደ ጉድጓድ ውስጥ ይወድቃሉ፡" አላቸው።

119 ወንድሞችና እህቶች ሆይ፡ እነሆ ወደዚያ ጊዜ እንደገና ተመልሰናል። እንደገና ወደዚያ ሰዓት ተመልሰናል። አስተውሉ። ለምን? ያው ለተመሳሳይ ምክንያት።

120 ባለፉት ዘመናት፡ ሰንኖርባቸው የነበሩት—እነዚህ ታላላቅ ብርሃኖች፡ ሁሉም ትክክል ነበሩ፡ በእነርሱ ላይ ምንም ተቃውሞ የለንም። ነገር ግን፡ በዚህ የሎዶቅያ የቤተክርስቲያን ዘመን፡ ተጠንቀቁ፡ አስታውሱ፡ ክርስቶስን-የማትቀበል ናት። አሁንም በትክክል ያችው ናት።

121 ይህ ታላቅ ካውንስል፡ ይህ የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴ፡ ፕሮቴስታንቶችን ሁሉ አንድ ላይ ለማሰባሰብ ዙሪያውን እየተንቀሳቀሰ ነው። ይህ የሚያደርገው ምንድን ነው? ራሱን ዋናውን ቃል፡ እያጨለመው ነው፡ ቃሉም ክርስቶስ ነው። እንዴት ይህንን ማድረግ ይችላሉ? ማለት፡ ክርስቲያን ሳይንስ፡ እና ዩናይትድ ብሬዘረን፡ እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች፡ አንዳንዶቹ በድንግልና መወለድን ያምናሉ፡ አንዳንዶቹ አያምኑም፡ አንዳንዶቹ **ይህንን** እና **ያንን** ያምናሉ። ራሳችሁን ካለማመን ጋር እንዴት ማያያዝ ትችላላችሁ? "ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ሊሄዱ ይችላሉን?" ከመካከላቸው ውጡ እና ተለዩ፡ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ይዛችሁ በእርሱ ጽኑ።

122 ኢየሱስ ክርስቶስ ቃሉን ለመግለጥ ግዴታ አለበት። ዛሬ የሚያስፈልገን የሚልክያስ 4 መነሳት ነው። ሌላ ነቢይ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይነሳል፡ እርሱም ቃሉ የገባውንም ነገር በትክክል ያደርጋል። ከዚያም፡ ሰዎች ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት፡ በጭፍን እርሱን ትተው በቀጥታ ወደ ጨለማው ይገባሉ።

123 አሁን፡ አስተውሉ፡ ዛሬም፡ ያው ተመሳሳይ ምክንያት ሆኖ፡ አይተነዋል፡ አብያተ ክርስቲያናት መልእክቱን ጠሉት፡ ቃሉን ሰቀሉት፡ ቃሉን አስወጥተዋል። አሁን የዚህ ካውንስል አባል ካልሆናችሁ፡ አትችሉም—የራሳችሁ ቤተክርስቲያን እንኳን ሊኖራችሁ አይችልም። ይዘጉታል። አባላቸው መሆን አለባችሁ። ካልሆናችሁ፡ ትዘጋላችሁ። ታዲያ ስለዚህ ጉዳይ ምን ትላላችሁ? ኦህ፡ እውነት ከሆነው ጋር ቁሙ! አስታውሱ፡ ዳግም፡ የመሰቀል ጊዜ ቀርቧል።

124 በቅርብ ጊዜ፡ በእንግሊዝ ውስጥ በዓለም ላይ ከታዩት ታላላቅ ዘረፋዎች—ታላቁን ዘረፋ ያስከተለው፡ ሐሰተኛው መብራት ነው። እስካሁን ከተፈጸሙት ታላቁ ዘረፋ የተደረገው፡ በሐሰተኛ መብራት ነው። ያንን ባቡር እንዲዘገይ ያደረገው የሰባት-ሚሊዮን-ዶላር ዘረፋ የተካሄደው በሐሰተኛ መብራት ነው፡ የስኮትላንድ ያርድ ፖሊስም ሰውየውን ማግኘት አልቻለም። በጣም በተንኮል፡ አመለጡ። ያም በዘራፊዎች ከተፈጸሙት ሁሉ የላቀ ዘረፋ ሆኖ ተቆጥሯል፡ በተፈጥሮው። ዓለም፡ በታላላቅ ዘረፋዎቿ ተዘረፈች።

125 በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ የተፈጸመው ታላቁ ዘረፋ ደግሞ፡ በሐሰተኛ ብርሃን፡ በሌላ ዘመን ነጸብራቅ፡ እና ለዚህ ዘመን የተተነበየውን ብርሃን ባለመቀበል ነው የተደረገው። አሜን። ሐሰተኛ ብርሃን፡ የትናንት ነጸብራቅ! በትናንት ነጸብራቅ ውስጥ አትመላለሱ። ዛሬ በልጁ ሙቀት ውስጥ ተመላለሱ። "የተአምራት ዘመን አልፏል፡" በማለት፡ ራሳችሁን ወደ የሐይማኖት ተቋም ጥላ ውስጥ አትጎትቱ።

126 ኢየሱስ፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፥ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ። እነዚህ ምልክቶች

ይከተሏቸዋል" አለ።

127 እንዲህ ይላሉ፡ "ለሐዋርያቱ ምንም ችግር የለውም፥ ለእኛ አይደለም።" ያ ነጸብራቅ ነው።

128 ኢየሱስም "ወደ ዓለም ሁሉ፡ ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡" ብሏል። አዎን፡ ወዳጄ።

129 ታዲያ ችግሩ ምንድን ነው? በነጸብራቅ ውስጥ መመላለስ፡ ታላቁን ዘረፋ አስከተለ፡ ክርስቶስን ከቤተክርስቲያን አውጥቶታል። አያችሁ፡ በዛሬው ዘመን ቃል የተገባውን ቃል፡ እንዴት ክርስቶስ ራሱን በትናንትና ቀዝቃዛ የሐይማኖት መግለጫ ሊገልጥ ይችላል? ዘሩን አያሞቀውም። አይ፡ ጌታዬ። የቤተክርስቲያን ታላቅ ዘረፋ!

130 ማሞቅ? ደግሞም፡ አስታውሱ፡ ያ የቀዘቀዘ የሐይማኖት መግለጫ ብርሃን የዛሬውን ዘር ፈጽሞ ሊያበስለው አይችልም። ዘሩን ይክደዋል። በምድር ላይ ያለው ጭጋግ፡ ችፍጉ። እግዚአብሔር የሚነሳበትና ብርሃኑን ዳግሞ የሚያበራበት፡ ቃሉንም ሕያው የሚያደርግበት ጊዜ ነው። በእርግጥም፡ ብርሃን! ያ የቀዘቀዘ የሐይማኖት መግለጫ እህሉን አያበስለውም። በእርግጥ አያደርገውም።

ደግሞም፡ አስታውሱ፡ የሥልጣኔ ጉዞ ከፀሐይ ጋር ነው።

131 በመጀመሪያ እንደነገርኳችሁ፡ የተፈጥሮን አካሄድ፡ ምሳሌዎችን እመለከታለሁ። ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ትምህርት የለኝም፥ አልፈልገውምም። በዓለም ላይ ካለው ትምህርት ሁሉ ይልቅ፡ ያለኝ ቢኖረኝ እመርጣለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ አለኝ። እርሱ ቃሉን እስከ መጨረሻው ሲኖርበት አይቻለሁ፡ ማወቅ የሚያስፈልገኝም ያንን ብቻ ነው።

132 ማንም ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ከሆነ፡ ለዛሬው ቀን መልስ መሆኑን ለማየት መጽሐፍ ቅዱስን ይመረምራል። የዘመኑ መልስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ቃሉ ነው። ቃሉ ሕያው ሲሆን፡ ለዘመኑ ተሰፋ የተሰጠውን ብርሃን ያሳያል። በዚህ ጨለማ የሎዶቅያ ዘመን፡ ጥቂቶቹ ብቻ፡ "እኔ የምቀበላቸውን ሁሉ፡ እቀጣቸዋለሁ፡ እገሥጻቸውማለሁ። ንስሐ ግቡ፡" "ተመለሱም፡" አለ ኢየሱስ። ወደ ቃሉ ተመለሱ። እርሱ ቃል ነው። ወደ እርሱ ኑ። አዎን፡ ወዳጄ።

133 ብርሃንን ተመልከቱት። ከምሥራቅ መጥቶ፡ ወደ ምዕራብ ይሄዳል። እኛም በምዕራብ ዳርቻዎች እንገኛለን። ሦስት ደረጃዎች ነበሩት፡ አይደል? ሦስት ደረጃዎች ነበሩት። ውሃውን አቋርጦ፡ ሦስት ጊዜ ተሻገረ። ከጳውሎስ ጀምሮ፡ ሜዲትራኒያንን አቋርጦ፡ ወደ ጀርመን ገባ፡ ጀርመን በሉተር በራች፥ የእንግሊዝን ቻናል አቋርጦ፡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስና አሁን... ወደ—ወደ እንግሊዝ ገባ፥ ከዚያም፡ እንግሊዝ፡ ፓሲፊክን አቋርጦ፡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መጣ። የሉተርን መልእክትን በመያዝ ጠንክራ ሰርታለች፡ በመጨረሻው ክፍልም፡ እዚህ በምዕራብ ጠረፍ ላይ እንደገና ደርሷል።

134 ከእህሉ መብሰል ጀምሮ፡ ከዚያ ከሉተር አንስቶ፡ እስከዚህ ዘመን ሁሉ ድረስ፡ ሊያበስል የሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል፡ የወንጌሉ ሙላት አሁን መሆን አለበት። በመጽደቅ፡ በመቀደስ፡ በጴንጤቆስጤ ዘመን በኩል የታየው

ብርሃን፡ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የሙሽራይቱን ዛፍ ሊያበስል ይገባዋል፥ ክርስቶስም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ፡ እንደ አንድ አካል፡ እርሱና ሚስቱ፡ እርሱና ሙሽራው ሆኖ መገለጥ አለበት። አሜን። አሁን የምንኖርበት ሰዓት ይህ ነው። የዘመኑ ብርሃን ይህ ነው። በእርሱ ተመላለሱ! “የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ሆይ፡ ዳኑ።”

135 የዘመኑ የቤተ ክርስቲያን ነጸብራቅ በጣም አሳሳች እንደሆነ፡ ኢየሱስ በማቴዎስ 24 ላይ ተናግሯል። እርሱም፡ “የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ ያስታል” ብሏል። አያችሁ፡ ሉተር አይችልም… ሉተር ሜቶዲስትን ሊያስት አይችልም። ሜቶዲስት ጴንጤቆስጤን ሊያስት አይችልም። ያ ትክክል ነው፡ አያችሁ፡ ነገር ግን ስለ ሙሽራይቱስ ምን ይባላል? የጴንጤቆስጤዎችን ዓይን ያሳወረው ያ ነው። አዎ። አያችሁ፡ ወደ ሐይማኖት መግለጫችሁ፡ ወደ ሥርዓታችሁ ተመለሳችሁ፡ ተደራጃችሁ፡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ የሚነግሯችሁንም የሰዎች መንጋ ሰበሰባችሁ።

136 መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች ተስፋ ይሰጣል። በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞሉ ወንዶችና ሴቶች ያስፈልጉናል።

137 የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ እንዳለ የምትናገሩ ከሆነ፡ እግዚአብሔርም እዚህ ውስጥ የተወሰነ ተስፋን ከሰጠ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ያንን እንዴት ሊቃረነው ይችላል፡ “አይ፡ ለሌላ ዘመን ትክክል ሊሆን ይችል ይሆናል። እኛ በዚያ መንገድ አናምነውም” ሊል ይችላልን? ያ መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

138 በእግዚአብሔር የተሞላ ሰው፡ እርሱና ቃሉ አንድ ናቸው። በእርግጥም፡ አንድ ነው። እርሱ የኅብረት ውጤት፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የኅብረት ውጤት ነው።

139 የአንድ ሰው ሚስት ልትሆን ያለች ሴት፡ እርሱ እንድታደርገው የማይፈልገውን ነገር እያደረገች፡ በተቃራኒው እያደረገች፡ እንዴት ትቃረነዋለች? ከዓለም፡ ከሐይማኖት ተቋማትና ከድርጅቶች ጋር እየተሽኮረመምን፡ እንዴት የሰዓቱን ብርሃን ውድቅ እናደርጋለን? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል፡ ወንድም እና እህቶች? ለእያንዳንዳችሁ ባለን አምላካዊ ፍቅርና አክብሮት፡ እነዚህን ነገሮች እንዴት እንቀበላለን? እንዴትስ እንስማዋለን? መልሶ በእኛው ጭን ውስጥ ይወድቃል።

140 ሉተራውያንን አትኮንኑ፥ ምክንያቱም፡ እነርሱ ካቶሊክን ኮንነዋልና። ዌስሊን አትኮንኑ፥ ምክንያቱም፡ እርሱ ሉተራውያንን ኮንኗልና። አያችሁ፡ ልክ እንደዚያው፡ ዛሬ እየሆነ ያለውን ነገር ስትኮንኑና ከእርሱ ስትመለሱ፥ አብያተ ክርስቲያናቶቻችሁ ወደዚህ ታላቅ የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴ ውስጥ ሲገቡ ስታዩ፡ እናንተንም፡ እያንዳንዳችሁን፡ ወደ አውሬው ምልክት እየመራችሁ፡ መሆኑን እያያችሁ፡ ተቀብላችሁታል። ብዙ ቅን-ልብ ያላቸው ሰዎች በቀጥታ ወደ እርሱ ይገባሉ።

እናንተም፡ “እነዚህ መልካም ሰዎች ናቸው፡ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው” ትላላችሁ።

141 እነዚያም ካህናት እንደዚሁ ነበሩ። የኢየሱስ ክርስቶስን ቅድስና፡ ወይም የመንፈስን ፍሬ መውሰድ ካለብኝ፡ ከእናንተ ብዙዎቻችሁ በዚህ ላይ ሄዳችኋል... አሁን፡ ይህን አትናቁት። እያንዳንዱን ቃል እምነዋለሁ።

142 ብዙዎች፡ "ኦህ፡ በልሳኖች ተናግሬአለሁ። አግኝቼዋለሁ" ይላሉ። እርሱ አይደለም። አይደለም፡ ወዳጄ።

ብዙዎቹ፡ "የመንፈስ ፍሬ፡ ይህ ነው" ይላሉ። ነውን?

143 እስኪ ኢየሱስን ለፍርድ እናቅርበው (እግዚአብሔር ሆይ፡ ይቅር በለኝ) ለአፍታ። እናንተን ላቅርባችሁ፡ እኔም ቄሱ ልሁን። እኔም እንዲህ እላችኋለሁ፡ "የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚባል፡ ይህ ወጣት ሰው፡ ወደ ከተማው መጥቷል። እርሱን አትስሙት። እኛ በመንፈስ ፍሬ እናምናለን። አሁን ይህ ደጉ አዛውንት ካህናችሁ፡ ተመልከቱት። እርሱ፡ አያቱ፡ ቅድመ-አያቱ፡ ሁሉም ካህናት ነበሩ። ወጣትነቱን ሁሉ፡ መስዋዕት አድርጓል። እዚያው ሴሚናሪ ውስጥ ቆይቷል። ጠብቋል፡ አምኗል፡ ያስተማሩትን ሁሉ አ—አድርጓል። መጽሐፍ ቅዱስን፡ ከሀ እስከ ፐ ያውቀዋል። እራሱም፡ ይጽፈዋል። መጻሕፍትን፡ እራሱ ይጽፋል፡ ጸሐፍት እንደሚያደርጉት። እናም ይህ ሰው፡ ታላቅ ሰው! መሆኑን ታውቃላችሁ።

144 "እናታችሁ እናንተን በምትወልድበት ጊዜ ምን ሆነ? በአልጋዋ አጠገብ የቆመላት ማን ነበረ? ያ ደጉ አዛውንት ካህን። እናትና አባት ሊለያዩ ሲሉ፡ በሁለቱም ላይ እጆቹን አድርጎ ወደ እግዚአብሔር የመለሳቸው ማን ነበረ? ያ ደጉ አዛውንት ካህን። አዎ።

145 "እንዲሁ ይሖዋም ስለ ኃጢአት መስዋዕት የሚሆን፡ በግ ይጠይቃል። የቢዝነስ ሰዎችም፡ እዚህ ከተሞች ውስጥ ይኖራሉ እ—እነርሱም ዕቃዎቻቸውን፡ እ—እና ሌሎችንም፡ ምርቶቻቸውንና ሸቀጦቻቸውን፡ እና ሊሸጡ ያሰቡትን ማንኛውንም ነገር ይሸጣሉ። በጎችን አያረቡም። ታዲያ ካህናት ምን አደረጉ? አንድ ሰው ገብቶ፡ ነፍሱን በይሖዋ ፊት እንዲያነጻ፡ እነርሱ በጎችን እንዲሸጡበት፡ አንድ ትንሽ ሱቅ እዚያ ላይ አዘጋጁለት።

146 "ይህ ሰው፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ፡ ያደረገው? ከየትኛው ቤተ ክርስቲያን ነው የመጣው? የየትኛው ሃይማኖት ተቋም አባል ነው? ምን ዓይነት የኅብረት ካርድ አለው? እነሆ እኛ እናስወጣዋለን። እርሱ እያንዳንዳችንን ይኮንናልና፡ እኛ ከእርሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለንም። ምን አደረገ? እርሱ ወደዚያ ወጣና ያንን፡ ሰዎች ነፍሶቻቸውን ለማዳን የሚሞክሩበትን፡ ቤተ ክርስቲያንን፡" ዛሬ እናንተ መንፈሳዊ-አእምሮ ያላችሁ ሰዎንች፡ እንደምትሉት፡ "ጠረጴዛውን ገለበጠ፡ ሳንቲሞቹን ወረወረ፥ ገመዶችንም ወስዶ ጎነጎነ፡ አባረራቸውም፥ ያንንም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው አዛውንቱ ካህናችሁን፡ 'የዲያብሎስ ልጅ' አለው፡ ችግር ውስጥ በነበራችሁ ጊዜ ገንዘብ ያበደራችሁን ያንን ደጉን አዛውንት እንደዚያ አለው።

147 "ከእናንተ ጋር የቆመው ማን ነው፡ በምትሞቱበትስ ጊዜ ማን ይቀብራችኋል? ደጉ አዛውንት ካህን። እርሱ የመንፈስ ፍሬ አለው። ዳሩ ግን ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ የመንፈስ ፍሬ አለው ወይ? "

148 በልሳኖች በመናገር ልትፈርዱ አትችሉም፡ እንዲሁም በመንፈስ ፍሬ ልትፈርዱ አትችሉም። ነገር ግን ወደ ብርሃን በመጣው፡ በእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ነው። ያንን የሚያደርገው ብርሃኑ ነው።

በዚያ ብርሃን ውስጥ የሚመላለሰው ሰው! ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቢያደርግም እንኳ፡ በልሳኖች በመናገር ላይ አልተመሰረተም ነበር። እርሱ ይህን ቢያደርግም እንኳ፡ የመንፈስ ፍሬ አልነበረም። በእርሱ ልትፈርዱት አትችሉም። ነገር ግን እርሱ እመነ አጸናውም፡ እግዚአብሔርም የዚያን ቀን የተሰፋ ቃል እያንዳንዱን ቃል በእርሱ ውስጥ ኖረበት። የዘመኑ ብርሃን ያ ነው። ማስረጃውም ያ ነው።

149 አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መውረዱ የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት ይክዳል ብሎ ሲነግረኝ፡ በእርሱ ላይ የሆነ የተሳሳተ ነገር አለ። በሴሚናሪዎቻችን፡ እንዲሁም በሌሎችም ነገሮች ላይ፡ ሰዎችን ይህንን የአእምሮ-እጥበት ቴዎሎጂና የዛሬውን ነገር ሁሉ ሲያስተምሯቸው የሆነ የተሳሳተ ነገር አለ። እነዚያ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያንኑ ያደርጉ ነበረ፡ ሰዎቹንም በቀጥታ ወደዚያ የኢኩሜኒካል እርድ ይመሯቸው ነበረ፡ ለምን፡ በእርግጥም፡ የተሳሳተ ነው።

150 ይህንን በጌታ ስም እናገራለሁ! የዘመኑ ብርሃን፡ የዘመኑ ብርሃን እውነት መሆኑንና አለመሆኑን፡ እናንተ ተመልከቱ!

151 እነዚያ ቀዝቃዛ የሐይማኖት መግለጫዎች ፈጽሞ መኸርን ሊያመጡ አይችሉም። በበጉ ደም የታጠበች፡ ከቃሉም ጋር አንድ የሆነች፡ ቤተ ክርስቲያን የሆነች ቤተ ክርስቲያን ሊኖረን ይገባል።

152 ኢየሱስ በዚህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ነጸብራቆች፡ በጣም አሳሳች መሆናቸውን ሲገልጽ፡ “ቢቻል ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ፡” ያስታሉ ብሏል። የተመረጡትን ብቻ! “ዳሩ ግን በኖኅ ዘመን እንደነበረው፡ ስምንት ነፍሳት እንደዳኑት፡ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል።” በዚያን ጊዜ የሚድኑት በጣም፡ በጣም ጥቂቶች ይሆናሉ።

153 ምን ያደርጋል? በቀጥታ ወደ እርድ ይመራል። አሁን እየኖርንበት ባለው በዚህ በአሁኑ ጨለማ ውስጥ ያንን እናገኘዋለን። ይህንን በመናገር፡ እደመድማለሁ። አሁን እየኖርንበት ባለው በዚህ የአሁኑ ጨለማ ውስጥ፡ አሁን እየኖርንባቸው ባሉት በእነዚህ ቀናት ውስጥ፡ ብርሃን በሰማያት በጠፋ ጊዜ፡ እዚህ መካከል ጠፍቷል፡ በፊታችን፡ ሊያሳየን፥ ምን እየተከናወነ እንደነበረ፡ በሰባቱ ማኅተሞች ላይ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አሳይቷል። እግዚአብሔርም ልክ በሰማይ ያወጀው፡ በቀጥታ ወርዶ በምድር ላይ ያውጀዋል። አብያተ ክርስቲያናትም ተንደርድረው ወደዚያ እየገቡ ነው!

154 ታዲያ ያቺን ቃሉን-የምትጠብቅ ትንሽ ሙሽራ ማን ያድናታል? ብቻዋን፡ ወደ ብርዱ ስትባረር ምን ይደርስባታል? አትበርድም፡ በዚህ ዘመን የተረጋገጠው የተሰፋ ቃል ናት። ኦህ፡ አዎ። ልክ እንደ...

155 አውቃለሁ፡ ለሰዎች፡ ቤተክርስቲያን ዝም ብላ፡ “እንግዲህ፡ ልክ ያው አንድ ዓይነት ነገር ነው” ስትል ማየት፡ ግራ የሚያጋባ ነው። ኢየሱስ እንዲህ እንደሚሆን ተናግሯል። “የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፡ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስት ድረስ፡” ይሆናል። ኦህ፡ አዎን። አዎን፡ ወዳጄ።

156 ይህ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ በፍሎሪዳ የነበረን አንድ ሰው ያስታውሰኛል። እያወራ ነበር፡ በፍሎሪዳ የተበላሸበት ሼቭሮሌት መኪና እንደነበረው፡ ወደ ጋራዥም እንደወሰደው ተናገረ። ይህ መካኒክም ነገሩን እያበጀው፡ ሁሉንም ነገር

በአንድ ላይ ገጠመው፡ ሊያስነሳው ግን አልቻለም። የቻለውን ሁሉ፡ አደረገበት። እነዚህን የተለያዩ ነገሮች ሁሉ አደሰ፡ ግን፡ የሆነ ነገር፡ ብቻ ሊሰራ አልቻለም። ሊያስነሳውም አልቻለም። ደጋግሞ መሞከሩን ቀጠለ። መካኒኩ ተደናግጦ፡ በሕንፃው ውስጥ ሁሉ፡ ይሮጣል፡ ይህንን ያንን ያነሳ ነበር።

157 ሰውየውም ቆሞ፡ “መኪናዬን እየጠበቅሁ ነው፡ ጌታዬ። አርፍጃለሁ። አታስነሳውም እንዴ፡” ይለው ነበር?

158 እርሱም፡ “የምችለውን ሁሉ እያደረግሁ ነው” አለ፡ በጣም ተደናግጦ እየሰራ ነበር። እናም ሄደ።

159 ወዲያው አንድ በጥሩ-ሁኔታ የለበሰ ክቡር ሰው መጥቶ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተው፡ ለመካኒኩም፡ ለጥቂት ጊዜ ጭንቅላቱን እንዲያዘዋውር ካደረገው በኋላ፡ እርሱ፡ “ይህን ለምን አትነካውም? ምንም የመሰመሩ ኃይል ተቋርጧል” አለው።

160 ስለዚህ እርሱም፡ “ያንን በፍጹም አላሰብኩትም ነበር” አለ። ስለዚህ እዚያ የነበረውን ነገር፡ ያንን ትንሽ ነገር አዞረው፡ መሰመሩም—ኃይል አገኘ፡ መኪናውም ተነሳ።

161 ዞር አለና፡ “አንተ ማን ነህ” አለው? ማን እንደነበረ ታውቃላችሁ? የ—የጀነራል ሞተር ዋና መሐንዲስ። ያንን ነገር የሰራው እርሱ ነው። ዲዛይን ያደረገው እርሱ ነው።

162 በዚህ ሰዓት፡ ወንድሜ፡ ሪቫይቫላችን ምን እንደነካው፡ ችግር ምን እንደሆነ ግራ ሰንጋባ? ቁሳቁሱና ሁሉም ነገር አለን፡ መካኒካዊ ክፍሎች አሉን፡ ዳሩ ግን ዳይናሚክሱ የት አለ? ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሰፍራው ለማምጣት፡ የሚያስፈልገን ያ ነው። ችግሩ ምንድነው? ልንገራችሁ፡ ዛሬ እዚህ፡ ዳይናሚክሱን መንካት የሚችል፡ ሃሌሉያ፡ መንፈስ ቅዱስ የሚባል አንድ አለ። እርሱ የሜካኒክሱ ዳይናሚክስ ነው።

163 ዛሬ እኛ፡ ጴንጤቆስጤዎች ቆመናል፡ በሀገሪቱ ካሉት ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነን፡ በየዓመቱም በሺዎች የሚቆጠሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ይጨመሩልናል፡ ዳሩ ግን ያ መንፈስ ቅዱስ የት አለ? እኛ በልሳን በመናገር፡ ተቀብለነዋል፡ እንዴት እንደሚሰራም አይተናል። ሜቶዲስቶች፡ በመጮህ ተቀብለውታል። ሉተር፡ በእምነት ተቀብሎታል፡ እንዲሁም ሌሎችም። ያ አይደለም እሱ።

164 ቃሉ ነው! የሚበራው ቃሉ ነው፡ ብርሃኑ በሜካኒክሱ ያበራል፡ እነርሱም ዳይናሚክስ ይሆናሉ። እነርሱ ዳይናሚክስ ናቸው፡ ዳይናሚክስ፡ ዳይናሚክስ ወደ መካኒክ ሲመጣ። ያንን ነገር ማንቀሳቀስ ይጀምራል። ያ ትክክል ነው። ቃሉን ውሰዱ። በእርሱ ላይ፡ የተዘበራረቀ አንድ ትንሽ ነገር ካለ፡ አይነሳም። ሽክሞን ሁሉ፡ ኑፋቄን ሁሉ፡ የሐይማኖት መግለጫን ሁሉ፡ አሰወግዱ፡ ያኔ ያ ዳይናሚክስ መንፈስ ቅዱስ፡ በቃሉ ውስጥ ሊፈስና የዚህን ቀን የተሰፋ ቃል ሊያረጋግጥ ይችላል፥ ያኔ ታላቂቱ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንደ ጄት አውሮፕላን በእግሮቿ ትቆማለች፡ ጌታዋንም ለመገናኘት ወደ ሰማይ ትነሳለች። ያ ፍጹም ትክክል ነው። ያንን እስክናደርግ ድረስ፡ አይሰራም። ነገሩ ይሄው ነው። አዎ፡ ጌታዬ። ማነው የሚያደርገው? በዚህ እያሰብንበት ባለነው ዘመን እርሱን የሚጠብቀው ማን ነው? አስታውሱ፡ ወንድሜ፡ አስታውስ።

165 አሁን ሌላ ትንሽ ታሪክ ያስታውሰኛል። ወደ ታሪኮች ለመመለስ አይደለም፡ ነገር ግን አንድ ጓደኛዬ ኒው ሜክሲኮ፡ ካርልስባድ ቆሞ ነበረ፡ እዚያ ካርልስባድ ስብሰባ እያደረግን በነበረበት ጊዜ። እዚያም ወደ አንድ ዋሻ ውስጥ የወረዱ ብዙ ሰዎች ነበሩ።

166 ኦህ፡ እ—እኔ ያንን ነገር ፈጽሞ ወድጄው አላውቅም፡ እዚያ ታች ጥልቀት ባለው ቦታ፡ ከመሬት በታች አንድ ማይል ያህል ርቀት ላይ ነው። እኔ፡ እኔ እዚህ ላይ መሆኔ ያረካኛል። በመሆኑም፡ እነርሱ በዚያ በኩል ወረዱ። እኔ ከፍ ማለት እፈልጋለሁ እንጂ፡ ዝቅ ማለት አልፈልግም። ስለዚህ እ...

167 ይህን ሰው ወሰዱት፡ ወደዚያም ወረደ። እርሱ ከአንዱ ጓደኛው ነበረ፡ ትንሿ ልጁና ትንሹ ልጁም አብረዋቸው ወረዱ። እ—እና እዚያ ታች ወደ አንድ ትልቅ ምድር ቤት ወረዱ፡ ኦህ፡ ከምድር ገጽ በታች በመቶዎችና በመቶዎችና በመቶዎች የሚቆጠሩ ጫማዎች ጥልቀት፡ ይመስለኛል፡ ታች ወረዱ። እናም ማብሪያው አጠገብ የነበረው ሰው፡ በድንገት [ወንድም ብራንሃም ጣቶቹን አጮኸ—እርታዒ።] ማብሪያውን አጠፋው። በዚያም እጅግ ጥቁርና ጨለማ ስለነበር፡ እጃችሁን እንኳ በፊታችሁ ሲንቀሳቀስ ማየት እስከማትችሉ ጨለማ ነበር። አንዲት ትንሽ ልጅ፡ ምስኪን ፍጥረት፡ በጣም ፈርታ ነበረ። በሙሉ ድምጿ፡ “ወይኔ፡ ጨልሟል! ጨልሟል! ጨልሟል፡” እያለች ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ መጮህ ጀመረች።

168 ትንሹ ወንድሟ ግን በአጋጣሚ ቆሞ ነበረ። በጨለማው ውስጥ ጮኸና፡ “ትንሿ እህቴ፡ አትፍሪ፡ መብራቱን ሊያበራ የሚችል አንድ ሰው እዚህ አለ፡” አላት።

169 ሃሌሉያ! ትንሿ ቤተ ክርስቲያን ምን ታደርግ ይሆን? አትጨነቁ። ዛሬ ብርሃኑን ሊያበራ የሚችል አንድ ሰው እዚህ አለ፡ እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኦህ፡ አዎን። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ!

170 አስታውሱ፡ ዕውሮቹ... በኢየሱስ ልደት ዘመን የ—የነበሩት ሀብታም ሰዎች፡ ስለ እርሱ እየጠየቁ፡ ወደዚያ ሰደርሱ ከኢየሩሳሌም ነጸብራቅ አልተወገዱም ወይም አልታወሩም። ቴዎሎጂያቸው—ቴዎሎጂያቸው ሊያብራራው አልቻለም። ነገር ግን ወደ ጎን ፈቀቅ ባሉ ጊዜ፡ ያንን የዘላለም ሕይወት ብርሃን ተከተሉት።

171 እናንተ የዛሬ ቢዝነሰሜን፡ የእነዚህን ድርጅቶች ነጸብራቅ አትመልከቱ፡ ዳሩ ግን ቃሉን አጥብቃችሁ ያዙ። ወደ ብርሃኑ ይመራችኋል። ትንሿ እህቴ፡ አትፍሪ፡ መብራቶቹን ሊያበራ የሚችል አንድ ሰው እዚህ አለ። ያኔ እንደነበረው ሁሉ ቃሉን ሕያው ሊያደርግ የሚችል፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን ራሱን ሊያረጋግጥ የሚችል ክርስቶስ እዚህ አለ። ታምናላችሁን?

እንቁም።

172 ወደ ቀጣዩ ስብሰባ ለመሄድ ጊዜው ከመድረሱ በፊት አሥራ አምስት ደቂቃ አለኝ። እጃችሁን አንሥታችሁ እንዲህ በሉ፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ብርሃኑን በእኔ ላይ አብራ። ቃሉን አምናለሁ። መካኒክሱን አምናለሁ። ጌታ ሆይ፡ ዳይናሚክሱን በውስጤ አስቀምጥ” ማለት ትፈልጋላችሁን? እጆቻችሁን አንሱና ወደ እርሱ ጩኹ፡ “ጌታ ሆይ፡ መብራቶቹን አብራ!” መብራቱን ሊያበራ የሚችል ሰው እዚህ አለ። በኮሙኒዝም ውስጥ፡ ሞተናል፡ በየዓይነቱ ባሉ

የድርጅቶች ደኅብያዎችም ተበልተናል፡ ዳሩ ግን መብራቶቹን ሊያበራ የሚችል አንድ ሰው እዚህ አለ። ያ ሰው መንፈስ ቅዱስ፡ ራሱ ነው፡ በመንፈስ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ!

173 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እነዚህ እጆች እያንዳንዳቸውን ዳሰስ፥ እጆችን ብቻ ሳይሆን፡ በክንዳቸው በኩል ወደ ልብ ወርደህ፡ የወንጌልንም ብርሃን አብራ። በኢየሱስ ስም!

64-0125 መብራቱን አብራው
ራማዳ Inn
ፊኒክስ, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org